CPJ

«የጸረ-ሽብርተኝነት ሕጉ የፕሬስ ደበልጥ ነፃነትን ይገድባል»

ሲፒጄ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የፃፈው ደብዳቤ

4

ሰላምና መረጋጋት ባቀናው አገር የገበያ መረጋጋት ይጠፋልን!?

አቤ ቶኪቻው

10

ኪዳን ተስፋሁን - የ2009 የዓለም ምርጥ ሞዴል

4




# አውራምባ ታይምስ

ለመረጃ ቅርብ ይሁኑ

2ኛ ዓመት ቁጥር 74 | ሐምሌ 21 ቀን 2001 | ዋጋ 3.50




## ሃይማኖት፣ ፖለቲካ እና ግብረገብነት

➤ መንግሥትና ሃይማኖት

3እና13



13

## ለቴዲ አፍሮ ክብር ልዩ ኮንሰርት ሊቀርብ ነው

*አዘጋጆች የመንግስትን ድጋፍ አግኝተዋል*



## የልዩነታችን ዋናው መነሻ

*«ኢህአዴግ መሪዎችን ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ለማሰር ሲያኮበኩቡና ቀን እየቀረጠ ለማስፈራራት ሲሞክር በፌራዊ የስራ አስፈጻሚ ኮሚቴው በ12 ድጋፍ በ1 ተቃውሞና በ1 ተአቅቦ ያሳለፈው ውሳኔ መሪዎችንን ለኢህአዴግ አሳልፎ የሰጠ የማይዘነጋ ታሪካዊ ክስተት ነው:: ይህ መልካም አጋጣሚ የተቸረው ኢህአዴግም መሪዎችን ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳን አስር በጨለማ ቤት ውስጥ ከረቸመባት:: እዚህ ላይ ነው እንገዲህ የልዩነታችን ዋናው መነሻ»*

8

*በውስጥ ገፅ*

(ሕግ አውጪ ? ሕግ አስፈፃሚ ? ሕግ ተርጓሚ) ?
➜ የመንግስት ውድቀት

ምርጫ ሲደርስ ፖለቲከኞች ኮሜድያን ይሆናሉ

## ኤዲቶሪያል

# ችግሮቻችን ሰው ሰራሽ ናቸው፤መፍትሄያቸውም ሰምና ወርቅ የለውም

ዛሬ በዓለማችን ላይ የሰብዓዊ ፍጡር የደህንነት ስጋት ምንጭ ከሆኑ ዋና ጉዳዮች ውስጥ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርና ከፍተኛ መጠን ያለው ስደት ተጠቃሽ ናቸው:: ዛሬ፤ በእያንዳንዷ ደቂቃ እጅግ በርካታ ቁጥር ያላቸው ሕፃናት ሰብዓዊነት በጐደለው መልኩ ለሽያጭ ይቀርባሉ፣ ሕግን ሽፋን ባደረገ የተድበሰበሰ የጉዲፈቻ ስምምነት ተላልፈው ይሰጣሉ እንዲሁም ከፈቃዳቸው ውጪ  ለዝሙት አዳሪነት ሕይወት ይዳረጋሉ::  ዛሬ በመላው ዓለም ያሉ ዜጎች፣ በተለይም አፍሪካውያን ከኢኮኖሚያዊ ማሕበራዊና ፖለቲካዊ ቀውሶች ጋር በተያያዘ አገራቸውን ጥለው ወደተለያዩ አካባቢዎች ይሰደዳሉ:: በዚህ ውል የለሽ ስደትም ስፍር ቁጥር የሌላቸው ምንዱባን ሕይወታቸውን ያጣሉ፣ እንዲሁም የደረሱበት ሳይታወቅ ባክነው ይቀራሉ:: አገራችን ኢትዮጵያም በዚህ አስከፊ ችግር ከተመቱ አገራት መካከል በመጀመሪያ ተርታ ትሰለፋለች:: በመሆኑም፣ ልንወያይበትና አጥብቀን የመፍትሄ አማራጮችን ልንሻበት ይገባል ብለን እናምናለን::

በሕገ-ወጥ አዘዋዋሪዎች፣ ሰብዓዊነት በጐደለው ተግባር፣ የወደፊት ሕይወታቸው የሚጨልመውን ንጹሀን ለመታደግ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና የድርጊት መርሀ ግብሮች ተቀርጸው በሥራ ላይ ቢውሉም ሚሊዮኖች ባልጠበቁት መንገድ የዘመናዊ ባርነት ሰለባ መሆናቸው አልቀረም:: እ.ኤ.አ በ2004 ኢትዮጵያ ሕገ-ወጥ የሰዎች ዝውውርን ለመከላከል የወጣውን የድርጊት መርሀ ግብር ተፈፃሚ ለማድረግ መንቀሳቀስ የጀመረች ቢሆንም ወንጀል የሚፈጸምበት ጥልፍልፍ መዋቅር ንጹሀኑን ሊታደጋቸው እንዳልቻለ ያሉት ጥናቶችና መረጃዎች ያመለክታሉ:: ጉዳዩ እጅግ አሳሳቢ ቢሆንም የተሰጠው ሽፋን ግን ሁነቱን የማይመጥንና ማሕበረሰባዊ ንቅናቄ በመፍጠር የለውጥ ብርሀን የሚፈነጥቅ አይመስልም::

በተደጋጋሚ ለመታዘብ እንደቻልነው ሁሉ፣ ይህ ለማሕበራዊ ቀውስ መንስኤነት እንደዋንኛ ነጥብ የሚታይ እንቅስቃሴ ብዙ ጉዳት ካደረሰ በኋላ በዘመቻዊ ርብርብ ለመከላከል የመሞከር ታሪክ እንዳይፈጠር ለማሳሰብ እንወዳለን:: በእርግጥ የተወሰነ መጠን ያላቸው የድርጊቱ ተዋናዮች ፍ/ቤት ቀርበው ውሳኔ ተላልፎባቸዋል:: ዘብጥያ ወርደው ሕግ የወሰነባቸውን እየተቀበሉ ነው:: ይሁንና የእጃቸውን አገኙ ብለን እጃችንን

አጣጥፈን የምንቀመጥበት ጊዜ እንዳልሆነ የሆኑትና እየሆኑ ያሉት ለሕሊና የሚሰቀጥጡ የጥፋት ድርጊቶች ያነቁናል:: ሊያነቁን ይገባልም እያልን ነው!

ስደትም የኢትዮጵያውያን መለያ እየሆነ ሄዷል:: የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ጉዳይ ኮሚሽን በየጊዜው የሚያወጣቸውን ሪፖርቶች የሚመለከት የውጭ ታዛቢ አገራችን በፕላኔታችን ላይ ለኑሮ አደገኛ ከሆኑ አካባቢዎች ዋነኛዋ እንደሆነች አድርጎ ሊያስብ ይችላል:: በየወሩ በሕገ-ወጥ መንገድ ድንበር የሚሻገሩ ዜጎቻችንን ቁጥር ያየን እንደሆን ሕዝባዊ ንቅናቄ ተፈጥሮ የአካባቢ ለውጥ የሚደረግ እንጂ ለስደት መንስኤ በሆኑት የኑሮ መሰናክሎች ያጋጠመ ክንውን አይመስልም:: በሁሉም ወገኖቻችን አማካይነት ነገን የተሻለ ለማድረግ የሚባጁ፣ የማህበራዊና ፖለቲካዊ ደህንነት ስጋት ውስጥ የወደቁ ዜጎቻችን ለአስከፊው የስደት ህይወት ይዳረጋሉ:: ከስደት በኋላስ? ብለን ግን ልንጠይቅ ይገባናል::

ከስደት በኋላ መንገዱ አባጣ ጎርባጣ የበዛበት፣ ዓለም አቀፍ የስደተኝነት ሕግን በፈረሙ አገራት ጭምር ከገቡበት ውል በተፃራሪ በመቆም እንግልቱን የሚያበዙበት፣ ከተጠበቁ ነገሮች ይልቅ ያልተጠበቁ ነገሮች የሚከሰቱበት መሆኑን የተወሰኑ የመገናኛ ብዙሀን ዘገባዎችን ብቻ በመመልከት መረዳት ይቻላል:: በኢኮኖሚያዊ፣ማሕበራዊና ፖለቲካዊ መንስኤዎች ቀያቸውን ጥለው በሌሎች አገራት የሚባዝኑት ዜጎቻችን ይህን መልእክት እያነበቡ ባሉበት ቅጽበት እንኳ ዋስትና በሌለው መንገድ ለገንዘብ ባደሩ የሰው ነጋዴዎች ከአንዱ ወደሌላው እየተነዱ ነው:: የሰብዓዊ መብት ጥሰት ወደሚፈፀምባቸው እስር ቤቶች እየተጋዙ ወይም በትናንሽ ጀልባዎች አደጋ የሞላባቸው ባሕሮችን ሲያቋርጡ ሕይወታቸውን እያጡ ነው:: በእርግጥ ሁኔታው አሳሳቢና የመፍትሄ መንገዶችን በሙሉ መፈተሽ እንዳለብን የሚጠቁም ነው:: ለምን? እንዴት? የሚሉትን መመለስ አለብን::

ለግማሽ ምዕተ ዓመት የዘለቀው የመጨረሻው ሰለሞናዊ ዙፋን በ1966ቱ አብዮት በተገረሰሰ ማግስት በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ አገሬንና ወገኔን የሚለው መንፈሳዊ ልዕልና ተገፎ ሕይወትን ለማቆየት የሚደረገው ሩጫ በየአቅጣጫው ቀጠለ:: ኢትዮጵያ የእድገቷና የለውጧ እምቅ ሀይል የሆነውን የተማረ የሰው ሀይል አጣች:: ሳይማር ያስተማረው ወገንም አመድ አፋሽ ሆነ:: የለውጡ ርዕይ ከልማት እመርታ ይልቅ የከብት ጭራ እየተከተለ እንዲቀይ በተፈረደበት የሚሊዮኖች ማሕበር ተገታ:: ዓመታት ነጐዱ:: ተስፋ ተሰንቆበት የነበረው አብዮት በደም መፍሰስ ተባጅቶ ማቆሚያ የለሽ ስደት አስከተለ:: ምዕራፉ መዘጋት ነበረበት፤ አልሆነም:: ዛሬም ስፍር ቁጥር የሌላቸው የእናት ኢትዮጵያ ልጆች የዚህ አስከፊ ሁነት ሰለባ ለመሆን ተገደዋል:: ለምን? ስንል የመጠይቁን ንጽረታዊ ገጽታዎችና የመፍትሄዎቹን አቅጣጫ ማመት ያስችላል ብለን እምናለን::

ማንም ጤነኛ አእምሮ ያለው ሰብዓዊ ፍጡር ስደትን እንደማይመርጥ እንገነዘባለን:: በተለይ «ነብር ዝንጉርጉርነቱን ኢትዮጵያዊም ኢትዮጵያዊነቱን

ይለቃልን?» በሚል ስር የሰደደ መንፈሳዊ ልእልና የተገነባ፣ ለአገሩ ፍቅር፣ ለሕዝቡ አክብሮት፣ ለባሕላዊና ታሪካዊ እሴቶቹ ስስት ያለበት ወገን ከመጠን ያለፈ ጫና ካልገጠመው ይህን መንገድ አይከተልምና የ«ለምን?» መጠይቃዊ ነፅሮት ምላሽ በዚህ ዙሪያ የሚያጠነጥን ይሆናል፡፡

ሶስት መሰረታዊ የስደት መንስኤዎች አሉ፡፡ ኢኮኖሚያዊ፣ ማለትም ለመኖር በቂ የሆነ ገቢ ከማጣት ወይም ከብቃትና ክህሎት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ክፍያ ማጣት፣ ማሕበራዊ፣ ማለትም በአንድ አገር ውስጥ ባለ የዘርፈ ሰብዕ መስተጋብሮች ከመገለል እስከ መጠቃት መድረስ፣ ፖለቲካዊ፣ ማለትም የመንግስትነት ሥልጣን ያለው አካል ከሚያወጣቸው ሕጎችና መመሪያዎች እንዲሁም ርዕዮተ-ዓለማዊ መስመር ጋር ተሳልጦ መጓዝ ካለመቻል እስከ አስከፊ ተጽእኖ ውስጥ መውደቅ ያሉት ናቸው፡፡ የእነዚህ ጭብጦች አሉታዊ ሽክርክር በቀጥታ ከመንግስት ጋር የሚያያዙ በመሆናቸው የተወሰኑ ነገሮችን ለማለት እንወዳለን፡፡

አገራችን በተፈጥሮ ሀብቷ የበለፀገች፣ የአፍሪካ የወንዞች እመቤት የምትሰኝ እንዲሁም ወደኢኮኖሚያዊ ሀብት ሊቀየር የሚችል ሀብት ቢኖራትም ስሟ ከርሀብና ድርቅ፣ ከድሕነትና እርዳታ ሰንጠረዥ ወጥቶ አያውቅም፡፡ የተትረፈረፈ ምርት በተገኘ ባቸው ዓመታት ጭምር በሚሊዮን የሚቆጠሩ እርዳታ ፈላጊዎች አሉ፡፡ የባሕላዊ ግብርና ሥርዓት የሚፈጥረው ፍልሰትና የተማረው ሀይል የሥራ አጥነት ቁጥር መናር በከፍተኛ አሀዝ ከሚያሻቅበው የሕዝብ እድገት ጋር የስደት አደጋ መፍጠሩ እሙን ነው፡፡ ስለዚህ መንግስት ለተከታታይ ዓመታት አስመዘገብኩት የሚለውን ኢኮኖሚያዊ እድገት ምንነት ከአጠቃላዩ አገራዊ የሁነት ጭብጥ ጋር በማነጻጸር አቋሙን እንዲመረምር፣ የአሀዙ እሳቤ ሁሉንም የሕብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ የሚያደርግ እድል የሚፈጥርበትን ፓሊሲ እንዲነድፍ ለማሳሰብ እንፈልጋን፡፡

የአገራዊ እድገት መገለጫ ሕንፃ መገንባታቸው፣ ብዙ ኦቶሞቢሎች በመዲናችን መንገዶች መሽከርከራቸው ወይም በረዥም ዓመታት ልጅ ልጆቻችን በሚከፍሉት እዳ የሚለካ ተደርጎ መሰላቱ ባለው ችግር ላይ መሳለቅ ካልሆነ ነባራዊ ሁኔታውን አይቀይረውምና ዘላቂ የሥራና የልማት ሁኔታዎችን በማመቻቸት በዚህ በኩል ያለውን የዜጎች እንግልት በአስቸኳይ እንዲያቆሙ ጠንካራ መልእክታችንን እናስተላልፋለን፡፡

ማሕበራዊና ፖለቲካዊ ቀውሶቹም ባሕላዊና ሳይንሳዊ መላ የሚያሻቸው ናቸው፡፡ ማሕበራዊ ቀውሶቹ በባሕልና በታሪክ ተሳስረው የኖሩ ወገኖች ውስጥ ጭምር ገብተው አሻራቸውን ሲያሳርፉ እያየን ነው፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ መንግስት ወገቡን አስሮ ባሕላዊ መላዎቹን መዳሰስ አለበት፡፡ በአብዛኛው ሰው ሰራሽ ችግሮች ናቸው፡፡ መፍትሄያቸው ሰምና ወርቅ የለውም፡፡ ይታሰብበት፣ እርምጃ ይወሰድ!!!

ቀደም ሲል እንደተመለከትነው ከፖለቲካ ያለመረጋጋት ጋር በተያያዘ የሚደረገው ስደት እንደአለመታደል ሆኖ ከአንድ ትውልድ በላይ እድሜ ፈጅቶም አላቆመም፡፡ ፓለቲካዊ ስደቶች የተለያየ ይዘትና ውስብስብ ሁኔታዎች እንዳለባቸው እንረዳለን፡፡

በመንግስት በኩል ግን ምሕዳሩን ካለማጥበብ በተጨማሪ የአመለካከትና የርዕዮተ-ዓለም ልዩነቶችን በተቻለ መጠን ለማቻቻል ከግማሽ መንገድ በላይ ሊጓዝ ይገባዋል እንላለን። የግማሽ መንገዱ ጉዞ በተደጋጋሚ ሲባል የምንሰማው አይነት ከመርህ ያላለፈ ሳይሆን ቁርጠኝነት የተሞላው ለነገይቱ ኢትዮጵያ የመሰረት ድንጋይ የሚጥል ይሁን። እነዚህ ግብአቶች ከተሟሉ ኢትዮጵያውያን በሚያፈቅሯት አገራቸው በመኖር ለወዳጇ ኩራት ለጠላቶቿ እሳት ይሆናሉ። ስደቱ ከተከሰተስ? ዜጎቻችን በዘርፈ ብዙ ችግሮች ለዚህ እጣ ከተዳረጉስ? ከማን ምን ይጠበቃል? ለነገ ሳንል የምንመልሰው ሊሆን ይገባዋል።

በዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት የስደተኞች ጉዳይ የሚያዝበት አያያዝ አለ። የቱንም ያህል ዜጎች በሕገ-ወጥ መንገድ ወደ አንድ አገር ይግቡ ግብረ ሰናይ ድርጅቶች ሁኔታውን ለመከታተል የሚጓዙበት መንገድ አለ። አንዳንዶቹ ድርጅቶች የተቋቋሙት ከስራ ፍለጋ ጋር በተያያዘ ከአገራቸው ውጪ  የሚደርሱባቸውን ጥቃቶች ተከታትሎ ተገቢውን እልባት እንዲያገኙ ማስቻል ቢሆንም የእለት ኑሯቸውን ለማሸነፍ በአረብ አገራት ሲንቀሳቀሱ በርካታ አስፀያፊ ድርጊትና ግድያ የተፈፀመባቸው ዜጎቻችን ደማቸው ደመ-ከልብ ሆኖ ሲቀር እያየን ነው። ከፍተኛ የገንዘብ በጀት፣ በቂ የሰው ኃይልና ችግሩን የመመርመር መብት ያላቸው ተቋማት ምን አደረጉ? የት ድረስ ተጓዙ? ይህን ጥቃት በሚፈጽሙት አገራት ፓሊስ፣ ፍርድ ቤቶችና ሕገ መንግስት የለም? መንግስትስ ምን አደረገ? ምን ያህል ተጽእኖ ፈጥሮ የዜጎቹ ገዳዮች ለፍርድ ይቅረቡ አለ? በአገሪቱ ውስጥ ያሉት ኤምባሲዎቻችንና ቆንቋስላዎች በዜጎች ላይ በሚደርሱት እንግልቶች ከሌሎች አገራት ጋር ሲነፃፁ የተለሳለሱ ናቸው የመባሉ ታሪክስ በተጠየቀ ትኩረት ተሰጥቶት የሚገታው መቼ ነው? እነዚህ አካላት ግዴታዎቻቸውን መወጣት እንዳለባቸው አበክረን እናሳስባለን። ለዜጎቻቸው ሕይወት ክብር ይስጡ፣ ተጠያቂነት እንዳለባቸውም አይዘንጉ።

በሌላ በኩል በተለያዩ ምክንያቶች ስደት የመጨረሻው አስከፊ እጣ ለሆነባቸው ዜጎቻችን አጭር መልእክት ማስተላለፍ እንወዳለን፤ የመጀመሪያው፣ ሁኔታዎቹ ፈታኝ ቢሆኑ እንኳ እስከመጨረሻው የተስፋ እንጥፍጣፊ ድረስ በኢትዮጵያ ሰማይ ስር ያሉ አማራጮችን እንዲሞክሩ ነው። ማንም ወዶ አገሩን አይለቅምና ይህ መሆኑ ግድ ከሆነ ግን በጥቂቱ ሁለት ነገሮችን ታሳቢ ማድረግ ያስፈልጋል። ስለሚጓዙበት አገር ያሉ መሰረታዊ ሁነቶች መረጃና ኢትዮጵያዊ ማንነትን የሚገልጽ ሰነድ (ፓስፖርት) ናቸው። በመጨረሻ፣ ግን ይህ ሁሉ ቀውስ ተወግዶ ዜጎች በአገራቸው ዘርፈ ብዙ ጉዳዮች ላይ ሙሉ ተሳታፊ በመሆን ኢትዮጵያን ጥለዋት የሚሄዱባት ሳይሆን ለሌሎች ጭምር ጥላ ከለላችን ብለው የሚመጡባት እንድትሆን ጥልቅ ምኞት አለን።

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር!!!

## verbatim

«ዶ/ር ሃይሉ አርአያ... የወ/ት ብርቱካን እስር የራሷ ጉዳይ እንጂ የፓርቲው እንዳልሆነ አድርገው የሰጡት መግለጫ እኛን ብቻ ሳይሆን መላውን የኢትዮጵያ ህዝብ ያሳዘነ ክስተት እንደነበር የሚታወቅ ነው፡፡ ሌሎች በጋዜጣ አይናገሩት እንጂ በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ የራስሽ ጉዳይ ነው ብለዋል»

**ወ/ሪት ብርቱካን ሚዴቅሳ ለእስር ሲዳረጉ የነበረውን ሁኔታ ምን እንደሚመስል በፕ/ር መስፍን ወልደማሪያም የሚመራውና በርካታ የስራ አስፈጻሚና የብሄራዊ ምክር ቤት አባላትን ያቀፈው ስብስብ ያወጣው መግለጫ**

«የውጪ ተዋጊዎች በከፍተኛ ሥልጣን አብረውት እየሰሩ መሆናቸውን አል ሻባብ አረጋግጧል ... የውጪ ተዋጊዎቹ የመጡት ከፓኪስታን እና ከአፍጋኒስታን ስለመሆኑ ጥርጣሬ አለን፡፡»

**ባንኪ ሙን**
**የተባበሩት መንግስታት ዋና ፀሐፊ**

**ባለፈው ሐሙስ አል ሻባብ በሰነዘረው ጥቃት 18 ሰዎች መሞታቸውንና 50 ሰዎች ደግሞ በጽኑ መቁሰላቸውን ተከትሎ ለሶማሊያ መንግስት ወታደራዊ ድጋፍ እንዲሰጥ ጥያቄ ባቀረቡበት ወቅት የተናገሩት፡፡**

«በአገራችን አንዱን ከሥልጣን አውርዶ ሌላ ለመሾም ሲባል ማዋረድ፣ የግል ህይወትና የቤተሰብን ጤንነት የሚጎዳ ነገር ሲፈፀምበት ለኖረው የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የካፍ ውሳኔ ትምህርት ሊሆን ይገባል፡፡»

**ዶ/ር አሸብር ወ/ጊዮርጊስ**
**የቀድሞው የኢትዮጲያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን ፕሬዝዳንት**

**አማተር አገልጋዮች ገንዘባቸውን፣ ጊዜያቸውንና ጉልበታቸውን ለእግር ኳሱ ማዋላቸውን ከግንዛቤ በማስገባት ለወደፊት በአገራችን ተመሳሳይ ክብር ሲሰጥ እንደሚገባ ለሪፖርተር ጋዜጣ የሰጡት አስተያየት፡፡**

# ዜናዎች

# ለቴዲ አፍሮ ክብር ልዩ ኮንሰርት ሊቀርብ ነው

## አዘጋጆቹ የመንግስትን ድጋፍ አግኝተዋል

**/በውብሸት ታዬ/**

ከተላለፈበት የእስር ውሳኔ አንድ ሶስተኛው በአመክሮ ከተነሳለት በቀጣዩ ወር የመጀመሪያ ሳምንት አካባቢ ይፈታል ተብሎ የሚጠበቀውን ድምጻዊ፣ የዜማና ግጥም ደራሲ የሆነው አርቲስት ቴዎድሮስ ካሳሁን /ቴዲ አፍሮ/ በክብር የሚቀበል ልዩ ኮንሰርት ለማቅረብ እንቅስቃሴ መጀመሩን የጀነሲስ ሚዩዚካል ኢንተርናሽናል በኢትዮጵያ መስራችና ዳይሬክተር የሆኑት አቶ እምላዕሉ ፍስሃ ለአውራምባ ታይምስ ገለፁ፡፡

የዩኔስኮ የባህል አማካሪ የሆነው ጀነሲስ ሚዩዚክ ኢንተርናሽናል 45 አባል አገራት ያሉት አለም አቀፍ ተቋም ሲሆን የኢትዮጵያዊውን አርቲስት የእስር ጊዜ ጠናቀቅ አስመልክቶ የክብር ግብዣው እንዲዘጋጅ ሃሳቡን ያመነጨው የተቋሙ የህዝብ ግንኙነት ኦፊሰር የሆነው ደቡብ አፍሪካዊው ማት ክላርክ መሆኑን ዋና ዳይሬክተሩ ገልፀዋል፡፡ እንደ አቶ እምላዕለ ገለፃ ማት ክላርክ በአርቲስት ቴዎድሮስ ካሳሁን የመዚቃ ስራዎችና የህይወት ታሪክ ዙሪያ ጥልቅ ምርምሮችንና በርካታ መረጃዎችን ያሰባሰበ ሲሆን ለኮንሰርቱ መሳካት የሚደረገው ጥረት በተቀናጀ መልኩ ቀጥሏል ብለዋል፡፡

በኮንሰርቱ ላይ ይቀርባል ተብሎ የታሰበው «ክላሲካል ኦርኬስትራ» ሲሆን ዝግጅቱ የተቋሙ ዋና መቀመጫ በሆነችው ቤልጅየም ሊቀርብ እንደሚችልና ለዚህም የድምፃዊው ሥራዎች የሆኑ የሙዚቃ ኖታዎች እንደሚላኩ አስታውቀዋል፡፡

አቶ እምላእሉ ስለ ክላሲካል ኦርኬስትራ ሲገልፁ «ይህ የሙዚቃ ስልት የሚቀርበው ጥናት በተደረገባቸው የሙዚቃ ሥራዎች ላይ ሲሆን በዝግጅቱ ላይ በጥቂቱ እስከ 45 የሙዚቃ መሳሪያ ተጫዋቾች ይሳተፋሉ፡፡ ቁጥሩ ከዚህ እጥፍ ሊሆንም ይችላል፡፡ እኛ እያደረግን ያለነው የቴዲ አፍሮን ጨምሮ ሌሎች የኢትዮጵያ መዚቃዎች ኖታ ተልኮ ልምምድ እንዲደረግ ነው፡፡ ይህ ለአርቲስቱ የሚደረገውን የክብር ግብዣ

ምሉዕ ከማድረግ በተጨማሪ የአገራችንን ሙዚቃ የምናስተዋወቅበት ይሆናል።» ብለዋል።

መቀመጫውን በቤልጅየም ያደረገው ጀነሲስ ሚዩዚካል ኢንተርናሽናል ሀገራችንን ጨምሮ ኮትዲቭዋር፣ ደቡብ አፍሪካና ኬንያ አባል አገራቱ ሲሆኑ በባህልና ኪነ ጥበብ የልምድ ልውውጥ የሚደረግበት አለም አቀፍ መድረክ መሆኑን አቶ እምላዕሉ ገልፀዋል። ከአመት በፊት 23 አገራት የተሳተፉበት የባህል መዚቃ ቱርክ ላይ ተደርጎ እንደነበር ያስተወሱት ዳይሬክተሩ በመድረኩ ላይ የተሻለ ተወዳዳሪ ሆኖ ለመገኘት ያሉትን አጋጣሚዎች በጥንቃቄ መጠቀም እንደሚገባ አሳስበዋል።

አርቲስት ቴዎድሮስ ካሳሁን ከእስር እንደተለቀቀ የክብር ግብዣውን ኮንሰርት ወደተግባር ለማምጣት የተለያዩ እንቅስቃሴዎች እየተደረጉ ነው ያሉት አቶ እምላእሉ «የባህልና ቱሪዝም ሚ/ር አስፈላጊው ትብብር እንዲደረግልን የድጋፍ ደብዳቤ በመጻፉ ማመስገን እንፈልጋለን» ብለዋል።

# «ሲቪክስ»፣ በ42 መያዶች ላይ የተወሰደውን እርምጃ አወገዘ

ዓለም አቀፉ የሲቪል ማሕበራት ተሚጋች «ሲቪክስ» /World Solidarity for Citizen Participation-CIVICUS/፣ የኢትዮጵያ መንግስት «ከስልጣናቸው ውጭ ተንቀሳቅሰዋል» ብሎ በ42 መያዶች ላይ የወሰደው የእግድ እርምጃ የሲቪል ማህበራትን እንቅስቃሴዎች የበለጠ ይገድባል ሲል እርምጃውን አውግዟል። የደቡብ መንግስት ባለስልጣናት የሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶችን የዘገቡ መያዶች የክልሉን ሰላምና ልማት ለማስተጓጎል ይሻሉ በማለት ወንጅሏቸው እንደነበር «ሲቪክስ» ጠቅሷል።

የ«ሲቪክስ» ሴክሬታሪ ጄኔራል ኢንግሪንድ ሲሪናታ፣ «የቅርቡ በመንግስት የተወሰደው እርምጃ ኢትዮጵያ እድገቱ በፍጥነት እየጨመረ ወደሄደ አምባገነንነት እየተጓዘች መሆኗን የሚጠቁም ሌላ ምልክት ነው።» በማለት እርምጃውን አስመልክተው ተናግረዋል። አያይዘውም፣ «ዴሞክራሲያዊ ተቃውሞን ለማፈን እና ሕዝባዊ ተቋማት ተጠያቂ ይሁኑ ሲሉ ድምፃቸውን የሚያሰሙትን ገሸሽ ለማድረግ ያልተፈነቀለ ድንጋይ የሌለ ነው የሚመስለው።» ብለዋል።

«ሲቪክስ»፣ የኢትዮጵያ መንግስት በመያዶቹ ላይ የጣለውን እግድ እንዲያነሳ እና የበጎ አድራጎትና ማህበራት እና የጸረ-ሽብርተኝነት አዋጆች ገዳቢ ጎኖቻቸው እንዲያሻሽል ጥሪውን አቅርቦለታል።

# ኪዳን ተስፋሁን - የ2009 የዓለም ምርጥ ሞዴል

የኢትዮጵያ የሚሊኒየሙ ንግስት (Miss Millennium Queen) ኪዳን ተስፋሁን የ2009 የዓለም ምርጧ እንስት ሞዴል ተባለች:: ሞዴል ኪዳን «Best Female Model of the World 2009» የተሰኘውን ስያሜ ያገኘችው «ሱኬር ሞዴልስ ኢንተርናሽናል» በአሊካንቴ፣ ስፔን ባሳለፍነው ዓርብ ባዘጋጀው የፋሽን ሞዴሎች ውድድር ነው::

የወድድሩ ዳይሬክተር እና መስራች ሱኬር ቫሌጆ ማርቴ «ወድድሩ የተፈጠረው በሀገር ውስጥ [በስፔን] እና በዓለም አቀፍ ለሚደረጉ የወደፊት ፕሮጀክቶች አዳዲስ መልኮችን እና ክህሎቶችን ለመሳብ» በሚል እሰቤ እንደሆነ ተናግረዋል::

የ24 ዓመቷ ሞዴል በበኩሏ ያገኘችው አዲስ ስያሜ በሞዴሊንግ ኢንዱስትሪው ለሚኖሩ የወደፊት ክንውኖች በራስ መተማመንን እንደጨመረላት ገልፃለች:: «ከዚህ በኋላ የሚያቅተኝ ይኖራል ብዬ አላስብም» የምትለው ኪዳን «በሙያው ተቀባይነት አግኝቻለሁ፣ ሁሌም ቢሆን [ተቀባይነት] ማግኘት እንደሚገባኝ አውቅ ነበር» ብላለች::

በሚሊኒየሙ ቁንጅና ውድድር ከተወዳደሩት በዚህ ዓመት ዓለም አቀፍ ውድድሮችን በማሸነፍ ሞዴል ኪዳን ተስፋሁን ሁለተኛዋ ነች:: የ19 ዓመትዋ በውነትዋ አበበ በ2009 በቻይና በተካሄደ ዓለም አቀፍ የቁንጅና እና የሞዴል ፌስቲቫል የአፍሪካ ሞዴል በመባል አክሊል ደፍታለች::

በ"Miss International 2007" እና በ"Miss Earth 2008" የሀገሯን ስም ማስጠራቷ የሚታወሰው የዓለም ምርጧ እንስት ሞዴል ኪዳን ተስፋሁን እዚህ ደረጃ ያደረሳትን ፈጣሪዋን አመስግናለች:: «ለመራኝ እና ህልሞቼ እውን እንዲሆኑ ላደረገው ለኃያሉ ጌታ ምስጋናዬ ከፍተኛ ነው::»

## መጣጥፎች

# ሰላምና መረጋጋት ባቀናው አገር የገበያ መረጋጋት ይጠፋልን!?

አቤ ቶኪቻው
abeto2007@yahoo.com

ቀጥሎ፣ ሰዉ በየ ጓዳው የሚያወራውን እኔ ጫካ አይደለሁምና እንደሚከተለው ግልፅ አድርጌ ለማውጋት እገደዳለሁኝ::

የኑሮ ነገር ዛሬም ሮሮ መሆኑ ቀጥሏል:: ብራችን እግሩ አልጠና እንዳለው ሕፃን «ወፌ ቆመች፣ ወፌ ቆመች» እያልን ብናባብለውም አቅም አግኝቶ ሊጠነክር አልቻለም:: «ድሮ ፓርቲ  የሚያስጨፍረን ገንዘብ ዛሬ ፓስቲ መግዛት አልቻለም!» እያለ ሰዉ ያወጋል::

በቅርቡ አንድ ወዳጃችን ሆቴል መመገብ ባቆመ በሶስት ይሁን በሁለት ዓመቱ አንድ ምግብ ቤት ገብቶ ምግብ አዘዘ:: ያዘዘው፣ ድሮ የለመደውን አይነት ምግብ ቢሆንም ሒሳብ ሲጠይቅ የተነገረው ግን ድሮ የሚያውቀው አይደለም:: በርግጥ ሁሉም ነገር ጨምሮ ጨምሮ የቀነሰው ፍቅርና መግባባት ብቻ መሆኑን ወዳጃችን አላጣውም:: ነገር ግን እንዲህ አይነት ጭማሪ ይኖራል ብሎ ባለማሰቡ፣ የምግቡ ሒሳብ በተነገረው ጊዜ በምግብ ቤቱ ያሉት ሰዎች ሁሉ ሒሳብ የተነገረው መስሎት፣ «የእኔን ብቻ ነው የጠየኩህ:: ሌሎቹ ሰዎች ራሳቸው ይከፍላሉኮ!» ብሎ ቢመልስም ከሁለት ዓመት በፊት ከጓደኖቹ ጋር ሳይሳቀቅ የሚበቃው ገንዘብ «ዛሬ ለአንድ ራሴ እንዴት አይበቃም?!» በሚል አለቅጥ መንግስትን ሲያማርር ሰምቼዋለሁኝ:: ይኸው ወዳጄ እየደጋገመ፣ «ይኼ መንግስት ነው ወይስ መቅሰፍት?» ሲል በሰማሁት ጊዜ ንግግሩ የጤና ስላልመሰለኝ ሙሉ ቀን ግምገማ ወፀሎት ሳደርግለትና ሒሱን ሳስውጠው ውያለሁኝ::

ባለፈው ምርጫ «መንግስት ለመመስረት የሚያስችለውን በቂ ድምፅ» ያገኘው ኢሕአዴግ፣ (በቅንፍ አንዳንዶች ኢሕአዴግ በቂ ድምፅ አገኘሁኝ የሚለው «በምርጫ ዘጠና ሰባት ሰዉ ምርጫው ተጭበረበረ በማለት ያሰማውን የጩኸት ድምፅ ነው::» ሲሉ ይደመጣል:: እኒህ «አንዳንድዶች» አክለውም፣ «የሰላማዊ ሰልፍ ጩኸት መንግስት ለመመስረት የሚያበቃ በቂ ድምፅ ከተባለ፣ እስቲ ጉድ እናድርገው ብለን በማሚያ ምርጫ ድምፃችንን አጠፋን:: አሁንም፣ «በቂ የጸጥታ ድምጽ አግኝቻለሁኝ!» ብሎ «መንግስትነቱን አጸና» ሲሉ ቢሰማም::) ከቅንፍ ውጪ፣ እሰይ ያጸና! እንዲህ ያለ ልማታዊ መንግስት እንኳዋስ እንዲህ የተለያየ ድምፅ አግኝቶ ይቅርና ምንም ድምፅ ሳያገኝ ሺህ ዓመት ቢነግስ ምን ይጎዳናል? ክፋት ነው እንጂ!

እና፣ በትረ ስልጣኑን በበቂ ድምፅ የጨበጠው መንግስት፣ በሰላምና መረጋጋት ስራ ከአገር ውስጥ አልፎ ተርፎ ሌሎች የአፍሪካ አገራት ላይ የሚነሳውን ግርግር ጸጥ ለጥ በማድረግ የተዋጣለት መሆኑ ይታመናል:: «ታድያ የሰላምና የመረጋጋት ሥራ ያልቸገረው መንግስት፣ የገበያና መረጋጋት ሥራ እንደምን ከበደው?!» እያለ ሰዉ በየጓዳው እያወራ ነው:: እኔ የመንግስቱ ወዳጅ ይህንን ጉምጉምታ አደባባይ ሳወጣ፣ ተናጋሪዎቹን መጠቆም ካስፈለገ፣ ከኔ በስተቀር ሌላው የአገሬው ሰው በሙሉ መሆኑን ለመጠቆም እወዳለሁኝ:: ከዚህ ጋር ተያያዞ ሌላም ሌላም ወሬ መዝግቤ ይዤለሁኝ፤ ወደ በኋላ ተመልሼ አወጋለሁኝም::

ወዳጄ እርስዎ እንዴት ሰነበቱ? እኔ «ችሎ ማደር» የምባል ወዳጅዎ፣ እነሆ ሁሉን ችሎ ማደር መልካም ነው ብዬ ብርዱን፣ ጨለማውን ባጠቃላይ ኑሮውን ችዬ ይነጋል፣ ይመሻል:: እተነፍሳለሁኝ ማለት ነው:: በቅርቡ አንድ የሃይማኖት ሰባኪ፣

«ትንፋሽ በፈረቃ ባለመሆኑ፣ ፈጣሪን አመስግኑ!» እያሉ ሲያስተምሩ ሰምቼ በእውነት ልቤ ተነካ!

እስቲ አስቡት?! ትንፋሽ እንኳንስ በፈረቃ ሆኖ ይቅርና «ያለማቋረጥ ተጠቀሙ፣ ነገር ግን ካርድ ሙሉ» ብንባል ምን ሊውጠን ነበር? «ያልዎት ቀሪ ሒሳብ አነስተኛ ነው፤ እባክዎን ከመተንፈስዎ በፊት ሒሳብዎን ያስተካክሉ» ቢሉን ጉድ ፈልቶ ነበራ! ስለዚህ መተንፈስን ያክል ነገር ያለ ካርድ፣ ያለ ፈረቃ የሰጠንን ፈጣሪ ማመስገን ተገቢ ነው:: እና፣ ተመስገን እያልኩኝ አለሁልዎ!

እኔ የምለው? ቴሌዎች በቅርቡ በሞባይል ስልኮቻችን አማካኝነት የኢንተርኔት አገልግሎት ተጠቃሚ ሊያደርጉን መሆኑን ሰምተናል:: እሰይ እንዲህ ነው እንጂ የአገልግሎትን አድማስ ማስፋት! «ከአግልግሎት መስጫ ክልል ውጪ ናቸው!» በሚለው ቃል አጋኖ የሚታወቀው ቴሌ፣ ዛሬ እንዲህ የአገልግሎት አድማሱን ለማስፋት ማሰቡ ያስመሰግነዋል:: በነገራችን ላይ፣ ቴሌ እንዴት ነው ነገሩ?! ስንት የተከበሩና ኃላፊነት ያላቸውን ሰዎቻችንን ሁሉ «ከአገልግሎት መስጫ ክልል ውጪ ናቸው!» እያላችሁ ሙልጭ የምታደርጉት ነገር ብዙም አልጣመኝም:: በቅርቡ፣ አንድ እጅግ የተከበሩ በሕዝብ ይሁንታ ስልጣን ላይ የወጡ «አንቱ» የተባሉ ሰው ጋ ደውዬ በተደጋጋሚ፣ «ከአገልግሎት መስጫ ክልል ውጪ ናቸው» የሚለው የቴሌ ምላሽ በሰማሁኝ ጊዜ ልማታዊው መስሪያ ቤት (ቴሌ) አሽሙር ጀመረ እንዴ?! ስል ጠርጥሬያለሁኝ::

እውነቱን ለመናገር፣ ቴሌንና መብራት ኃይልን አንድ የሚያመሳስላቸው ነገር እየተከሰተልኝ መጥቷል - የያዙትን አገልግሎት በአግባቡ ሳይሰጡ የማስፋፋት ስራ ለመስራት እሽቅድድም ማድረግ:: መብራት ኃይልም እንዲሁ ቀድሞ መብራት «ለሰጣቸው» ሰዎች በአግባቡ በፈረቃው እንኳ ማዳረስ ተስኖት በዜና ላይ ስንሰማ፣ አዳዲስ ቦታዎችን «የሃያ አራት ሰዓት (ይመስለኛል የአራት ሰዓት ለማለት ነው፤) ተጠቃሚ አደረኩኝ» እያለ ሲል ያስቃል:: (ያሳቅቃል ማለቴ!) አሁን ቴሌም ይኸው «ለአስቸኳይ መልክት ሞባይል ከመደወል ሮጥ ብሎ መንገር ይቀላል::» በሚባልበት በዚህ ጊዜ፣ ኢንተርኔት በሞባይል ሊጀመር መሆኑ ይቺ ነገር ለሪፖርት ግብዓት ትሆን ይሆንን? ስንል ልንጠራጠር እንገደዳለን::

ከላይ እንዳወጋነው ብዙዎች፣ «ገንዘባችን አቅም አነሰው:: ገበያው ሊረጋጋ አልቻለም::» እያሉ አለቅጥ ሲማርሩ በሰማሁኝ ጊዜ፣ ምንም እንኳ ንግግራቸውና የበዛ ማማረራቸው በቀደሙት መንግስታት ቢሆን ኖሮ ለእስር የሚዳርጋቸው አይነት ቢሆንም አሁን የእስር ጊዜ ቀርቶ የምክር ጊዜ ተተክቷልና እኒህን ሰዎች ስመክር ከርሜያለሁኝ::

አንዱ ወዳጃችንን በተለይ፣ «ተው አብዝተህ አታማር፤ ገንዘብኽ ያልበቃህ የገንዘቡ አቅም ማጣት ወይም ደግሞ የገበያው አለመረጋጋት ሳይሆን ከአጠቃቀም ጉድለት ሊሆን ይችላልና እራስህን መመርመር ነው ያለብህ» ብለው፣ «ራሴን እነደምን ልመርምር?» የሚል የብልህ ጥያቄ ጠይቆኝ ነበር:: እኔም፣ «ለምሳሌ ሱሶችህን መቀነስ . . .» ብዬ ገና ከመጀመሬ፣ «ልክ ብልሀል:: ሱስ ነው ዋናው ችግሬ:: ልክ ነህ ሱሴን ወይ ቀንሳለሁኝ

ወይ እተዋለሁኝ። ልክ ነህ . . . እግዚአብሔር ይስጥህ! እግዜር ያክብርህ!» እያለ ደጋግሞ ቢያመሰግነኝ፣ ነገሩ ጥርጣሬ አሳደረብኝና፣ «ሱሶችህ ምን ምን ናቸው?» በማለት ጠየኩት። «አንደኛው ሱሴ በጾበልም፣ በጸሎትም፣ በምንም ሊተወኝ ያልቻለው እንጀራ ነው። ይሄን እንጀራ የተባለ ሱሴን ካልተውኩኝ ኑሮን አልቻልኩትም። ሁለተኛው ሱሴ፣ ትራንስፖርት ነው። ወደ ቤትም ሆነ ወደ ሥራ ለመሄድና ለመምጣት ትራንስፖርት የመጠቀም ከፍተኛ ሱስ አለብኝ። ይህን ሱስ ለማርካት ስል በርካታ እዳ ገብቻለሁኝ፤ ምክንያቱም፣ የወር ደሞዜ እንኳንስ ወር ይቅርና ሳምንት አትቆይማ! አሁን ገና ገባኝ! ለካስ ገንዘባችን ዋጋ አጣ እያልን የምናማርረው አለአግባብ ኖሯልና! ሱሳችን በዝቶ ነውና! ሌላው ሱሴ ቤት ኪራይ መክፈል ነው። ሌላም ሱስ አለብኝ፤ ጸጉሬ ሲያድግ የመቆረጥ ሱስ . . . » እያለ እያለ ማለቂያ የሌለውን የዕለት ተለት ኑሮውን ሁሉ ቢዘረዝርልኝ በጣም ተበሳጨሁኝና፣ «እኔ ያልኩህ፣ ለምሳሌ ትጠጣ እንደሆን . . . ?» ብዬ ስጀምር፣ የሰውን እልህ እንጂ ንግግር የማያስጨርሰው ወዳጄ፣ «ትጠጣ እንደሆን አልከኝ?» አለና በጥያቄ ጀመረልኝ፤ «መጠጣትማ ጥሩ ነበር። ችግሩ፣ «እሺ» ብለው አይታዘዙህም። እንጂማ «እሺ» ብለው ቢታዘዙ፣ አንድ ሽጉጥ ያለ በረዶ አዘህ መጠጣት! ከዛ፣ ከዚህ ሁሉ መከራ ግልግል!» ቢለኝ፣ «ሆድ ለባሰው አለመታዘዝ ነው» የምትል ጥቅስ ነገር በአዕምሮዬ መጣች።

**በመጨረሻም 1ኛ፡- አፋልጉኝ! ሳሚ እና ሆሊፊውድን ያያችሁ . . .**

በዛን ሰሞን ከቴሌቪዥን፣ ሬድዮና ጋዜጣ አልፎ ተርፎ፣ በየታክሲው ላይና በየቡናው ሁሉ ጨዋታ ማድመቂያ የነበረው የሳሚና የሆሊፊውድ ቦክስ ውድድር (ዕቅድ) ነበር። ውድድሩ ይዘጋጅ የነበረው፣ (የነበረው ልበል እንጂ! መቼም እንዲህ ከረሳነው በኋላ አይጫወቱም!) ኤች. አይ.ቪ.ን ለመዋጋት የገንዘብና የግንዛቤ አስተዋጽኦ ለማበርከት ነበር። (ገንዘቡን እንኳ ትተን ለግንዛቤ ብንል ይሻለናል፤ ምክንያቱም አንዳንድ ክፉ የመረጃ ሰዎች እንደሚያወሩን ከሆነ፣ ሆሊፊውድ በአገሩ ከኪሳራው ብዛት ንብረቱ በጨረታ እየተሸጠ ባለበት በዚህ ወቅት፣ ይሄን ገንዘብ አሳልፎ ይሰጣል ማለት ሞኝነት ነው!)

የሆነ ሆኖ፣ በርካቶቻችን ውድድሩ ለአገራችን መልካም ገፅታ የሚኖረውን ፋይዳ እያሰብን የውድድሩን ቀን በጉጉት ስንጠባበቅ ከርመናል። ምንዋጋ አለው?! «ሳሚ ከዚህ በፊት ሳይነኩት የሚወድቅ «መንገደኛ ፈረንጅ» አምጥቶ በዝረራ አሸነፈ» እያሉ ሲቧልቱ ለነበሩ ሰዎች ይግረማችሁ ብሎ ሳይወዳደር የሚጠፋ ሌላ ፈረንጅ ይዞላቸው መጣ! በበኩሌ፣ በሰላማዊ ትግል የማምን ሰው ነኝና ሳሚ እና ሆሊፊውድ መቧቀሱን ትተው በጠረጴዛ ዙሪያ ችግራቸውን ቢፈቱ የበለጠ ደስ ይለኛል። ነገር ግን ሌሎች ቦክስ ወዳጆች በዛን ሰሞን፣ «ሆሊፊውድ አዲስ አበባ ገባ» (ይሁን ሊገባ ነው) ከሚለው ዜና ጀምሮ የጨዋታውን መጀመር በንቃት ሲጠባበቁ ነበርና ዛሬ ሳሚንም ሆነ ፈረንጁን ቢያጧቸው፣ «አፋልጉኝ! ሳሚና ሆሊፊውድ ለቦክስ ውድድር ብለው ቢወጡም መድረኩ ላይ የሉም» አይነት ማስታወቂያ ሊያወጡ አስበዋል።

**በመጨረሻም 2ኛ**

አዲስ አበባ ላይ ብቻ ይሁን በሌሎችም የአገራችን ከተሞች እንዲህ ይደረግ ባይገባኝም፣ አንድ አሳሳቢ ነገር በመዲናችን አብዝቶ እየተከናወነ ይገኛል:: «ምን?» አይሉኝም:: በመኪና ላይ ትልቅ ስፒከር እየሰቀሉ አንድ ጊዜ መንፈሳዊ፣ ሌላ ጊዜ አለማዊ፣ ደሞ ሌላ ጊዜ ፖለቲካዊ፣ አሁንም ሌላ ጊዜ ሎተሪያዊ የሆነ አጀንዳ እየያዙ ከተማውን የሚቀውጡ ሰዎች ጉዳይ በእውነቱ እያሳሰበኝ ነው::

በርካታ ጊዜ ይህ አይነቱ «ቅወጣ» የሚደረገው በከተማው አስፋልቶች ላይ ነው:: ታድያ በርካታ ማየት የተሳናቸው ወዳጆቻችን ይህ ቀውጢ «ሙዚቃ» የተሸከርካሪ አደጋን በቀላሉ እንዳይቆጣጠሩ ያደርጋቸዋል:: በፊት ክላክስም ይሁን የመኪና ማንኛ ውንም ድምጽ በመስማት መንገድ ለመሻገር ምንም የማይቸገሩ እኒህ ወዳጆቻችን፣ «ካለኔ አትስሙ!» የሚለው ሙዚቃ፣ ችግር እየፈረጠረባቸው መሆኑን እያወጉን ነው::

እኔ በበኩሌ የችግሩን ፈጣሪዎች ለመምከር ባደረኩት ጥረት «መንፈሳዊያኑ»፣ «አንተ አሕዛብ» ሲሉኝ፣ አለማዊ ካሴት ነጋዴዎቹ፣ «አንተ ደስታ የራቀህ» ሲሉኝ፣ ተቃዋሚ ፖለቲከኞቹ «አንተ ካድሬ» ሲሉኝ፣ «ግብር አስከፋዮቹ» «አንተ ህገ ወጥ» ሲሉኝ፣ ባለ ሎተሪዎቹም «አንተ ገደ ቢስ» እያሉኝ ምክሬን የሚሰማኝ አጥቻለሁኝ:: ስለዚህ፣ ሁሉም የየበኩሉን ሙዚቃ እየከፈተ ከተማዋ ወደ ትልቅ ጭፈራ ቤት ከመቀየሯ በፊት፣ በተለይ ማየት በተሳናቸው ወዳጆቼ ስም የሕግ ያለህ! እላለሁኝ::

ወዳጄ እነሆ «ሲኖሪና ቻው ቻው!» የምንባባልበት ቦታ ላይ ደርሰናል:: የሰማነውን በልቦናችን ያሳድርልን::

አማን ያሰንብተን!

# ሃይማኖት፣ ፖለቲካ እና ግብረገብነት

በመክብብ ማሞ
(mekbma@yahoo.com)

ሰሞኑን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤ/ክ የተፈጠረው ግርግር የብዙዎቻችንን ቀልብ የሳበ መሆኑ ዕሙን ነው:: ወደ ግርግሩ በመግባት ዝርዝር ማብራሪያ ለመስጠት አልፈልግም፤ የሙያው ብቃትም ሆነ ዕውቀት የለኝም:: ሆኖም ግን በዚህ ጽሁፍ ለማተኮር የፈለኩት ፍትሕንና የሰብዓዊ መብትን በተመለከተ የሃይማኖት መሪዎች እስከምን ድረስ መሄድ ይጠበቅባቸዋል የሚለውን ነው::

እንኳንስ ገና የዴሞክራሲ ምንነት በሥርዓት ባልተለመደባት አገራችን ኢትዮጵያ ይቅርና በሰለጡትና የዴሞክራሲ ፋና ወጊ ነን በሚሉት ምዕራባውያን አገሮችም ውስጥ ሃይማኖት እና የሃይማኖት መሪዎች በፖለቲካና መንግሥት አስተዳደር ውስጥ ቁልፍ

ሚና አላቸው:: ይህ ልምድም ከጥንት ዘመን ጀምሮ ሲሰራበት የቆየ ሲሆን በተለይም በመካከለኛው ዘመን የካቶሊክ ቤ/ክ በአውሮፓ የነበሩትን መንግሥታት በቀጥታ የማዘዝ ሥልጣን ነበራት:: ይህንን ሥልጣን ጳጳሱ በመጠቀም ነገሥታትን ይሾምና ይሽር እንደነበር ከታሪክ እንረዳለን::

በ11ኛው ክፍለ ዘመን መጠናቀቂያ አካባቢ በጀርመኑ ንጉሥ ሔንሪ እና በሮማው ጳጳስ ግሬጎሪ መካከል በተፈጠረው አለመግባባት ምክንያት «ንጉሡ የጳጳሱን ሥልጣን ተጋፍቷል» በሚል ከቤ/ክ በተወገደ ጊዜ፣ እዚያው ሮም ድረስ ሄዶ ይቅርታ እንዲጠይቅ በተደረገበት ተጽዕኖ ምክንያት ወደዚያው ያቀናል:: ሮም ከደረሰም በኋላ ሦስት ቀን ሙሉ በአውሮፓ ብርድና በረዶ እየተንገላታ የጳጳሱን ደጅ ከጠና በኋላ ነበር ይቅርታን ያገኘው:: (አንዳንዶችም ባዶ እግሩን በረዶ ላይ ቆሞ ይቅርታን እንደጠየቀ ይናገራሉ::)

በዘመናችንም በአውሮፓም (ራሺያን ጨምሮ) ሆነ ሰሜን አሜሪካ እንዲሁም ሌሎች አገሮች የሃይማኖት መሪዎች በመንግሥት አሰራር ላይ ተጽዕኖ የማድረግ ኃይል እንዳላቸው በተደጋጋሚ የሚስተዋል ተግባር ነው:: ይህም ከግብረሰዶማውያን «ጋብቻ» ጀምሮ እስከውርጃ፣ የሞት ቅጣት፣ ወዘተ ድረስ የሕግ አወጣጥንም ሆነ ፖሊሲ ቀረጻን ወደሚፈልጉት አቅጣጫ ሲዘውሩት የሚስተዋል ነው::

ወደአገራችንም ስንመጣ ቤተክህነትና ቤተመንግሥት ለዘመናት የተሳሰረ ግንኙነት እንዳላቸው እንረዳለን:: ነገሥታት ወደዙፋናቸው ሲወጡ በቤተክህነት አንጋሽነት ነበር ሥልጣናቸውን የሚረከቡት:: የቤተክህነት መልካም ፈቃድና ድጋፍ የሌለው አጼ አልጋው አይረጋም፣ የግዛት ዘመኑም አይረዝምም:: ይህም በአጼ ቴዎድሮስ ዘመን የታየ ሲሆን ንጉሡ ተግባራዊ ማድረግ የጀመሩትን አዲስ የመንግሥት መዋቅርና የቤ/ክ አስተዳደር በመቃወም የቤተክህነት መሪዎች ቁልፍ ሚና ተጫውተዋል:: ይኸው የቤተክህነት የበላይነት እስከ አጼ ኃይለሥላሴ ዘመነ መንግሥት የዘለቀ መሆኑ የብዙዎቻችን የቅርብ ጊዜ ትዝታ ነው:: ሆኖም ግን ኢትዮጵያ ከአጼ ሥርዓት ተላቃ ወታደራዊው ደርግ ሥልጣኑን በተረከበ ጊዜ በቤተመንግሥትና በቤተክህነት መካከል የነበረው ግንኙነት መልኩን በመቀየር ቤተክህነት ቀጥታ የሥርዓቱ ተገዢ እና አስፈጻሚ መሆን ጀመረች:: በዚህም ምክንያት ደርግ ቤተክህነትን በእጁ በማስገባቱ ለዓመታት ያሻውን ሲያደርግ፣ ሲያስር፣ ሲገድል ወዘተ ከቤተክህነት በኩል የተሰነዘረበት ምንም ዓይነት ጠንካራ ተቃውሞ አልነበረም:: እንደ ሰማዕቱና ጀግናው አቡነ ጴጥሮስ «ውጉዝ ከመአርዮስ . . . » በማለት በድፍረት ያወገዘው የሃይማኖት አባት ባለመኖሩ በወዲ ዜናዊ ዘመንም ይኸው ሊቀጥል ችሏል:: ለዓብነት ለመጥቀስ ያህልም ከምርጫ 97 በኋላ በተፈጠረው አለመረጋጋት የጸጥታ ኃይሎች በሰልፈኞች ላይ ጉዳት ሲያደርሱ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙት ዋና ዋና ሃይማኖቶች - የክርስትና እና (የኦርቶዶክስ ተዋህዶና ሁሉንም ፕሮቴስታንቶችን ጨምሮ) የእስልምና ሃይማኖት መሪዎች መካከል በድፍረት ወጥቶ ይህንን ተግባር የተቃወመ አልነበረም::[1] አሁንም እየተደረገ ስላለው

አፈና፣ የሰብዓዊ መብት ጥሰት፣ . . . ከየትኛውም የሃይማኖት አባቶች በኩል የሚሰማ ምንም ነገር አለመኖሩ የሃይማኖት መሪዎች የሞራል ዝቅጠት ጉልህ ማስረጃ ነው::

የሮማው ሊቀጳጳስ ቤኔዲክት ከሶስት ሳምንት በፊት ያወጡት ባለ 50 ገጽ ሰርኩላር (Papal Encyclical) ነበር:: ይህ ሰርኩላር «በጎነት በእውነት» (CARITAS IN VERITATE) ተብሎ የተሰየመ ሲሆን በጽሁፉም ላይ ስለ ፍቅር (በጎነት) ሲናገሩ፣ «ፍቅር ሰዎችን ስለፍትህና ሰላም በድፍረትና በጽናት እንዲቆሙ የሚያደርጋቸው ልዩ ኃይል ነው» ይላሉ:: ሲቀጥሉም፣ «ይህ ፍቅር ሰዎችን ከፈጣሪቸው ጋር በማስተሳሰር ከቤተሰቦቻቸው፣ከወዳጆቻቸውና ከሚጎዳኙት ቡድን ጋር በደቂቅ (micro) ደረጃ የሚያስተሳስራቸው ብቻ ሳይሆን በማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ በልሂቅ (macro) ደረጃም የሚያስተሳስራቸው እንደሆነ ይጠቅሳሉ:: «እውነት የሌለበት ፍቅር ወደ ስሜታዊነት አዘቅት የወረደ ከመሆን ያለፈ ብቻ ሳይሆን ባዶም ነው:: እውነት በሌለበት ባሕል ውስጥ ፍቅር ለሞት የሚያደርስ አደጋን ይጋፈጣል» በማለት የፍቅርንና የእውነትን (ሃቅ) ግንኙነት ጽሁፉ ካስረዳ በኋላ በማስከተልም ሲቀጥል፣ «ዓለማችን አንድ እየሆነች ባለችበት ባሁኑ ጊዜ ለሰዎች ዕድገት ልዩ አትኩሮት ሊሰጣቸው ከሚገባቸው ነገሮች መካከል አንዱ ፍትህ» እንደሆነ የሚገልጽ ሲሆን፣ «ፍትህ ደግሞ ፍትህን እንደሚሻ» ያስረዳል:: ይህም በፍትህ ውስጥ ያለ ፍቅር «የሰዎችን ህጋዊ መብት ማወቅና ማክበርን እንደሚጠቀልል እና በዚህች ምድር ላይ የሚገኝ ማናኛውንም አገር በሕግና በፍትህ ለመገንባት ጥረት እንደሚያደርግ» ጽሁፉ ያብራራል::

ይህንን ሃሳብ ይዘን አሁን አገራችን ወዳለችበት ሁኔታ ስንመጣ፣ የአገራችን ሕዝብ በአሁኑ ጊዜ በሰብዓዊ መብቶች ጥሰቶች እና በፍትሕ አልባነት ውስጥ እንዳለ የምንሰማው እውነታ ነው:: ከእነዚህ መካከል አንዷ ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ ለዓብነት የምትጠቀስ ናት:: ይህች የሰላማዊ ትግል መሪና የሕግ ተገዢ ሌላ አሳዳጊ ወላጅ ከሌላት ልጇና ጧሪ ከሌላቸው እናቷ ተለይታ ለወራት በእስር ስትቆይ፣ «እየተፈጸመ ያለው ነገር ተገቢ አይደለም» ብሎ የተቃውሞ ድምፁን ያሰማ የየትኛውም ሃይማኖት አባት (መሪ) አለመኖሩ የሃይማኖት መሪዎቻችንን ምን ያህል በፍርሃት የተተበተቡና ሞራላቸው ምን ያህል የላሸቀ መሆኑን በግልጽ የሚያሳይ ነው:: ይህንን ተግባር መቃወም አንዳንዶቹ «በመንግሥት (በፖለቲካ) ሥራ ውስጥ እኛ መግባት አንችልም» በማለት ከንቱ ምክንያት በመስጠት ለማሳመን እንደሚሞክሩት ሳይሆን ፈሪና ለሥርዓቱ ሰጥ ለጥ ብለው መገዛታቸውን የሚያሳዩበት ጉልህ ማስረጃ ነው:: ይህንንም በማድረጋቸው ምዕመኖቻቸውንና ተከታዮቻቸውንም እንዲሁ በፍርሃት አፋቸውን ለጉመው እንዲገዙ እያደረጉ መሆቸውን ሳይረዱት የሚቀሩ አይመስለኝም::

ኅብረተሰብ የሚመራበት የሞራል (ግብረገብ) እና የፍትህ መመሪያ በአብዛኛው ምንጩ ሃይማኖት ነው:: ሆኖም ግን አሁን ባገራችን ባሉት ዋናዋና ሃይማኖቶች ውስጥ ያሉ መሪዎች ለጥቅም የተገዙና እርስ በርሳቸው በዘር፣ በጎሳ ወዘተ ተከፋፍለው

እየተፋለሙ ባሉበት ወቅት በእነዚሁ የሃይማኖት መሪዎች መካከል የታጣውን እውነትን ፣ መከባበርን ፣ ሃቀኝነትን ፣ ወኔ ሙሉነትንና የዓላማ ጽናትን ከፖለቲካ መሪዎቻችን መጠበቅ ከንቱነት ነው::

የሁለቱንም አካሄድ በአሁኑ ወቅት በግልጽ እያየነው ያለ ነው:: የሃይማኖት መሪዎች ለእውነት፣ለሃቅና ለፍትሕ ሲቆሙ በማይታይበት ሁኔታ ላይ ሕዝብ ከከንፈር ያላለፈ «ፍቅር» ማሳየቱ ለምን ይገርመናል? ይህ ፍቅር አልባነት ባዶነትንና ወኔቢስነትን ከማስፋፋቱ ባሻገር የራስን ጥቅም የማሳደድ ጭፍን አመለካከት ውስጥ የሚጥል ሲሆን፣ ለሃቅና ለፍትህ የሚቆሙ ሰዎችን እንደ ሞኝና አላስተዋይ ወደመቁጠር እንደሚዘቅጥ እሙን ነው:: ህዝብ ከሃይማኖት መሪዎቹ ግብረገብነትንና ለሃቅ መቆምን ካልተማረና ይህንንም ደግሞ በፋና ወጊነት የሚያሳየውና መሪ ካላየ ቀስ በቀስ የአንድ አገር ህልውና ወደማክተሙ መሄዱ አይቀሬ ነው:: በእንደዚህ ሁኔታ ውስጥ የሚገኝ ሕዝብም «ፍትሕ ይገባኛል፤ የሰብዓዊ መብቴ ሊከበር ይገባዋል» ብሎ ለመብቱ ለመቆም ገና ረጅም ጉዞ ይቀረዋል:: ስለዚህም ታላቁ መጽሐፍ እንደሚለው (ሚክ. 7:4 እና 6:8)፣ «ከመካከላችን ያለው እጅግ ጨዋና ታማኝ የተባለው ሰው ከአሜኬላና ከኩርንችት በማይሻልበት» ዘመን የሃይማኖት መሪዎቻችን «ፍርድን ያደርጉ ዘንድ እና ምሕረትን ይወዱ ዘንድ» እንዲሁም ስለ እውነትና ስለ ፍትሕ እንደ አቡነ ጴጥሮስ በድፍረት ይቆሙ ዘንድ ሕዝብ ይጠብቅባቸዋል::

# «የጸረ-ሽብርተኝነት ሕጉ የፕሬስ ነፃነትን ይገድባል»

ሲ.ፒ.ጄ. ለጠቅላይ ሚኒስትር መለስ የፃፈው ደብዳቤ

ዓለም አቀፉ የጋዜጠኞች መብት ተከራካሪው ሲ.ፒ.ጄ. (Committee to Protect Journalists) ባሳለፍነው ረቡዕ ሐምሌ 15 ለኢትዮጵያው ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በፃፈው ደብዳቤ አዲሱ የጸረ-ሽብርተኝነት አዋጅ መፅደቁን ተከትሎ በኢትዮጵያ በፕሬስ ነፃነት ላይ የሚደረጉ ገደቦች እየጨመሩ መምጣታቸው እጅጉን እንዳሳሰቡት ገልጸዋል:: ሲ.ፒ.ጄ. ለጠቅላይ ሚኒስትሩ የፃፈውን ደብዳቤ እንደሚከተለው ተርጉመን አቅርበነዋል::

የተከበሩ ጠቅላይ ሚኒስትር፣

ይህንን የምንጽፍልዎ በኢትዮጵያ የፕሬስ ነፃነትን ይበልጥ ሊገድብ የሚችለው ሕግ እና ባለማቋረጥ እየተካሄዱ ያሉት የወንጀል ክሶች፣ አስተዳደራዊ ገደቦች እና የድረገጾች ግደባዎች እጅጉን እንዳሳሰቡን ለመግለጽ ነው:: በኦፊሴላዊ ማሳመኛ መግለጫዎች «ሕገ መንግስታዊ ሥርዓቱን» የሚያስጠብቁ ፖሊሲዎች እንደሆኑ ይፋዊ ማረጋገጫ የሚሰጥባቸው እነኚህ እርምጃዎች በተግባር ግን ገለልተኛ የፖለቲካ

ዘገባዎችን የሚወነጅሉና በኢትዮጵያ ሕገ መንግስት ዋስትና የተሰጠውን የፕሬስ ነፃነት የሚጥሱ መሆናቸው አሳስቦናል። ይህንን ሁኔታ ለማስቀረትም ባለዎት ኃላፊነት ተፅዕኖ ያደርጉ ዘንድ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

የፕሬስ ነፃነትን ጨምሮ መሰረታዊ ሕገ መንግስታዊ መብቶችን የሚገድቡ ጥቅል ድንጋጌዎችን በተመለከተ ከሕግ ባለሙያዎች፣ ከሕግ አውጪዎች፤ እንዲሁም ከግል ፕሬስ ተቃውሞዎች እየተነሱ ባለበት ሁኔታ የኢትዮጵያ ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጁን በሰኔ 30 አጽድቋል። የመንግስትን ጥቃት በመፍራት ስማቸው እንዳይጠቀስ የጠየቁ የተለያዩ ጋዜጠኞች የፀደቀውን ሕግ ለሚመለከቱ ትችቶች የሚሰጡትን ሽፋን ለመገደብ ከመንግስት ኃላፊዎች እና ከመንግስት ደጋፊዎች የስልክ ጥሪዎች እና ማስጠንቀቂያዎች እንደሚደርሷቸው ለሲ.ፒ.ጄ. ገልፀዋል።

አዋጁ ለአስፈፃሚው አካል የአሸባሪ ተግባራትን «የሚያነሳሱ፣ የሚደግፉ ወይም የሚያበረታቱ» የተባሉ ጽሁፎችን «የፃፈ፣ ያዘጋጀ፣ ያተመ፣ ያሳተመ፣ ይፋ ያደረገ፣ ያሰራጨ» ማንኛውንም ሰው እስከ 20 ዓመታት ድረስ ለማሰር ሰፊ ሥልጣኖችን የሚሰጡ ሩቅ-ደራሽ ድንጋጌዎችን አካትቷል። ይህ ሕግ መንግስት «አሸባሪ» ሲል ለሰየማቸው ቡድኖች ይጠቅማሉ ባላቸው ዘገባዎች ላይ ቅድመ ምርመራን ተቋማዊ ያደርጋል። ይባስ ብሎም ለፌደራል ፖሊስ እና ለብሔራዊ ደህንነት አገልግሎት ያለፍርድ ቤት ትዕዛዝ መገናኛዎችን መጥለፍ፣ እንዲሁም የሽብርተኝነት ተግባር በሂደት ላይ ነው ወይም ይፈፀም «ይሆናል» በሚል «ምክንያታዊ እምነት» ላይ በመመስረት ብቻ ፍተሻ እና ብርበራ የማካሄድ ሥልጣንን ሕጉ ይሰጣቸዋል።

ሕጉ በሽብር የተጠረጠሩ ሰዎች ክስ ሳይመሰረትባቸው ለአራት ወራት ያክል በእስር እንዲቆዩም ይፈቅዳል። ይሁንና በሶማሊያ በሽብርተኝነት ተጠርጥረው «ከተያዙ» 41 ሰዎች መካከል የኤርትራ መንግስት የቴሌቭዥን ጋዜጠኞች እንደሆኑ የታወቁትን ሳላህ ኢድራስ ጋማ ወይም ተስፋልደት ኪዳኔ ተስፋዝጊ በ27 ወራት እንኳን መንግስት ወደ ፍርድ ቤት ገና አልወሰዳቸውም። የኢትዮጵያ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እነኚህን እስሮች ለተመለከቱ የሲ.ፒ.ጄ. የመረጃ ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት በተደጋጋሚ ፈቃደኛ አልሆነም።

የመንግስት ቃል አቀባይ በረከት ስምዖን ሕጉ ከመጽደቁ አስቀድሞ አስተያየታቸውን ሲሰጡ አላግባብ የመጠቀም ሁኔታዎች እንደማይኖሩ ገልፀዋል። «ይህ ለሕገ መንግስታዊ ድንጋጌዎች የሚተጋ መንግስት ነው፣ እናም በሕገ መንግስቱ ማንኛ ውም ዓይነት ሥልጣንን አላግባብ መጠቀም አይፈቀድም» ሲሉ ለዓለም አቀፉ ብሮድካስተር ለአሜሪካ ድምጽ (ቪ.ኦ.ኤ.) ተናግረዋል። ሆኖም እነኚህ ዋስትናዎች ቢኖሩም ወሳኝ ዘገባዎችን መሰረት አድርጎ በገለልተኛ ፕሬስ ላይ የወንጀል ክሶችን ከመመስረት የመንግስት የረጅም ጊዜ አሰራር ጋር እና በእንዲህ ያሉ ጉዳዮች ላይ ከኢትዮጵያ ዳኛዎች እና አቃቤ ሕጎች ተሞክሮ ጋር ሲነፃፀር የዚህ ሕግ አላግባብ ተፈፃሚ የመሆን አቅሙ ከሁሉም የበለጠ አስጨናቂ ነው። እንደየሕግ ባለሙያዎች እና

የሲ.ፒ.ጄ ጥናት ከሆነ የፀረ-ሽብርተኝነት አዋጁም ሆነ በሥራ ላይ ያለው የወንጀል ሕግ የመንግስት አቃቤ ሕጐች በፕሬስ ላይ በሚመሰረቱ ክሶች ዓላማን (Intent) እንዲያረጋግጡ በመርህ ደረጃ ከፍተኛ መስፈርቶችን አስቀመጠዋል:: ይሁንና ግን በተግባር የኢትዮጰያ ዳኛዎች ለእነዚህ መስፈርቶች ጥቂት ወይም ምንም ግምት በመስጠት ለዘብ ባለ መልኩ ሲተረጉሟቸው ቆይተዋል::

ሲ.ፒ.ጄ. የመንግስትን አቋሞች ወይም መግለጫዎች የሚቃረኑ ወይም የሚያፋጥጡ ዘገባዎችን በማቅረባቸው የመንግስት አቃቤ ሕጐች ጋዜጠኞች ላይ በወንጀል ሕጉ «በሀሰተኛ ዘገባ ሕዝብን በማነሳሳት» ወንጀል ክስ የመሰረቱባቸውን ጉዳዮች መመዝገቡን ቀጥሏል:: የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች እንደሚሉት የኢትዮጵያ ዳኞዎች እንደ ከሳሹ ሁሉ የመንግስትን አቋሞች ወይም መግለጫዎች ጥያቄ ውስጥ ባለመክተት ሚዛናዊ ያልሆነ ንፁህነትን የማረጋገጥ ሁኔታ በተከሳሽ ገዜጠኞች ላይ በመጫን እንዲህ ያሉ ጉዳዮች እንዲቀጥሉ ሲፈቅዱ ቆይተዋል:: በተጨማሪም ጋዜጠኞችን ለማሰር እና የፓፕ ሙዚቃ አቀንቃኙ የቴዎድሮስ ካሳሁን የፍርድ ሂደትን ጨምሮ ጠንካራ የፖለቲካ ይዘት ባላቸው ዘገባዎች ላይ ቅድመ ምርመራ ለማድረግ ዳኛ ዎች «ችሎት የመዳፈር» ክሶችን የተጠቀሙባቸው የተመዘገቡ ጉዳዮችም አሉን::

ባለፈው ዓመት ከኒውስዊክ ጋር ባደረጉት ቃለ ምልልስ የኢትዮጵያ አዲሱ የፕሬስ ማሻሻያ ሕግ «የዓለም ምርጥ ከሚባሉት ጋር የሚስተካከል» ሊሆን የመቻሉን ተስፋ ገልፀው ነበር:: በየካቲት 19 በመንግስት ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽ/ቤት በተሰጠ የፕሬስ መግለጫ መሰረት ሕጉ «የሚዲያ መስፋፋትን ለማረጋገጥ እና ለአጠቃላይ ሚዲያው እንቅስቃሴ ገለልተኛነት ተገቢውን የሕግ ጥበቃ ለመስጠት» የታለመ ነው:: ሆኖም ከሁሉም አኳያ የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነፃነት አዋጅ ዓለም አቀፍ መመዘኛ ዎችን ለማሟላት እጅጉን ይሳነዋል:: ሕጉ ከዚህ ቀደም የነበሩ የስም ማጥፋት ቅጣቶችን ሲያጠነክር፣ ለብሔራዊ ደህንነት ሲባል ማንኛውንም ህትመት በአፋጣኝ የማስቆም ሥልጣንን ለመንግስት አቃቤ ሕጐች ይሰጣል፤ ነገር ግን የጋዜጠኞችን ቅድመ ችሎት እስራት ይከለክላል፣ ቢያንስ በመርህ ደረጃ::

ሲ.ፒ.ጄ. ባደረገው ጥናት መሰረት በዚህ ዓመት አራት የአማርኛ ቋንቋ ሳምንታዊ ጋዜጦች አዘጋጆች በወንጀል ክሶች አማካኝነት ከሦስት እስከ 16 ቀናት በእስር ቆይተዋል፤ ሁለቱ አሁንም በክስ ላይ ናቸው:: እንዲሁም ሌሎች የተለያዩ ጋዜጠኞች በክስ ላይ ሲሆኑ እንደ ጥናታችን ከሆነ ለፓለቲካ ተቃዋሚዎች ያመዝናሉ በተባሉ ዘገባዎች ሳቢያ የወንጀል ክሶች፣ የፖሊስ ምርመራዎች፣ አልያም የመንግስት ማስጠንቀቂያዎች ሊገጥሟቸው የመቻላቸውንም እድል ይጋፈጣሉ:: መንግስት የረጅም ጊዜ የመክሰስ ተሞክሮውን ቀጥሎበታል:: አሁን በማይታተመው ሰይፈ ነበልባል ጋዜጣ አዘጋጅ የነበረው አስራት ወዳጆ ከአራት ዓመታት በፊት በታተመ ጽሁፍ ሳቢያ በወንጀል ጉዳይ በመጋቢት ወር ፌዴራል ፍርድ ቤት ቀረቧል፣ የሀገር ውስጥ ጋዜጠኞች እንደገለፁት::

የየካቲት 19 ኦፊሴላዊ መግለጫ «የተለያዩ የሀሳቦች እና የመረጃዎች ነፃ ፍሰትን ለማረጋገጥ» የአስተዳደሩን ቁርጠኝነት ገልጿል። ሆኖም በጥር ወር የመንግስት መስሪያ ቤት የሆነው የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለስልጣን ሚዲያን የመቆጣጠር ሥልጣን ተሰጥቶታል። ባለስልጣኑም «የዜናዎችን እና የአመለካከቶችን መመሳሰል ለማስቀረት» በሚል ከሁለት በመቶ የባለቤትነት ድርሻ በላይ ያለውን ማንኛውንም የሚዲያ ባለቤት የአዘጋጅነት ሥልጣን እንዳይኖረው የሚያደርግ በፕሬስ ሕጉ ያልተካተተ የአፈፃፀም ማብራሪያ በአፋጣኝ አውጥቷል፣ እንደሀገር ውስጥ የዜና ዘገባዎች ከሆነ። በሚያዝያ ወርም ኤጀንሲው ለሦስት ጋዜጠኞች - አለም አቀፍ ተሸላሚዋ አሳታሚ ሰርካለም ፋሲል፣ ባለቤቷ አምደኛ እስክንድር ነጋ፣ እና አሳታሚ ሲሳይ አጌና - በአሁኑ ሰዓት የተቋረጡት አሳታሚ ድርጅቶቻቸው በ2007 ፀረ-መንግስት መሆንን በተመለከቱ ክሶች ስለተወሰነባቸው ፍቃድ ከልክሏቸዋል። የጋዜጠኞች እስክንድር ፍሬው እና መለስካቸው አመሀ ከሀገር ውስጥ የመዘገብ እውቅናን ካነሳ በኋላም በሰኔ ወር የግል ሬዲዮ ጣቢያ የሆነውን ሸገር ሬዲዮ ከቪ.ኦ.ኤ. እየተቀበለ የሚያስተላልፋቸውን ፕሮግራሞች እንዲያቆም ትዕዛዝ አስተላልፏል። መለስካቸው አመሀ የዓመታት እድሜ ባላቸውና ከታክስ ጋር በተያያዙ ክሶች አማካኝነት ለእስር ተዳርጎ ነበር። በኋላም በነፃ ተለቋል።

ከዚህ በተጨማሪ የእርሶ መንግስት የእኛን ጨምሮ ድረ-ገጾችን የማጣራት ሥራውን ቀጥሎበታል፤ በተለይም መቀመጫቸው በውጭ ሀገር የሆኑ የፖለቲካ ማሻሻያዎችን እና ሰብዓዊ መብቶችን የሚያወያዩ ገለልተኛ ድረገጾች እና ብሎጉችን አግዷል።

በፀረ-ሽብርተኝነት አዋጁ እና በመገናኛ ብዙሃን እና የመረጃ ነፃነት አዋጁ ውስጥ የተካተቱ የፕሬስ ነፃነትን ሕገ መንግስታዊ መብቶች የሚሸረሽሩ ድንጋጌዎች ላይ ማሻሻያ ይደረግባቸው ዘንድ በአፅንዖት እንመክራለን። በፍትህ ሥርዓቱ አተገባበር እና ጋዜጠኞች ክስ በሚመሰረትባቸው የወንጀል ድንጋጌዎች አፈፃፀም ላይ ገለልተኛ ግምገማ እንዲያካሂዱ፣ እንዲሁም ገለልተኛ የሚዲያ ተቆጣጣሪ አካል መፈጠርን እንዲያረጋግጡ እንጠይቃለን።

በሀገርዎት በጋዜጠኝነት ሙያ ነፃ ትግበራ ላይ ያሉትን ሁሉንም ገደቦች ያነሱ ዘንድ እንጠይቆታለን።

ከአክብሮት ጋር

**ጆዔል ሲሞን**
**ኤክዚኩቲቭ ዳይሬክተር**

# ስመሆኑ አዲስ አበባ ተቆጣጣሪ አላት?

**በናፍቆት ዮሴፍ**

ከተማችን አዲስ አበባ ስሟን ለመምሰል ለዘመናት መድከም ግድ ይላታል:: ስለከተማዋ ዘርፈ ብዙ ችግሮች በተለያዩ ብዙሀን መገናኛዎች ብዙ ተብሏል:: ነገር ግን እስካሁን ጠብ ያለ መፍትሔ አልተገኘም:: ታዲያ ችግር እንደአሸን እየፈላባት ያለችን ከተማ «አዲስ አበባ» ብሎ መጥራት ማሽሟጠጥ አይሆንም ትላላችሁ?

ወዲህ ለመንገድ ስራ በከተማዋ የተለያዩ ቦታዎች ታርሰው ሕዝቡን በበጋ አቧራው፣ እነሆ አሁን ደግሞ በክረምቱ ጭቃው ያሰቃየዋል:: ስለመፀዳጃ ቤቶቿም ብናወራ ከሁሉም የበለጠ ራስ ምታት ነው:: በኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት በኩል ብንሄድ በወር ውስጥ 15 ቀን የኃይል አቅርቦት የሚጠፋባት በዓለም የመጀመሪያዋ ከተማ ሳትሆን እንደማትቀር እገምታለሁ:: ውሀም ቢሆን በአራት እና በአምስት፣ አለፍ ሲልም በሳምንት አንድ ጊዜ ብቻ የሚያገኙ የከተማዋ አካባቢዎች እንዳሉ ምስክር መጥቀስ ወይም ጥናት ማድረግ አያሻውም:: በተለይ የኃይል አቅርቦቱ ነገር ለብዙ ድርጅቶች መዘጋት እና ለስራ ተፈናቃዮች መብዛት መንስኤ ሆኗል:: ታዲያ ይህቺ ከተማ ተቆጣጣሪ ወይም አስተዳዳሪ አላት ብሎ አፍ ሞልቶ ለመናገር እንዴት ይቻላል?

ይህን ከላይ የገለጽኩትን ጽሁፍ ለማስፈር የተገደድኩበት ምክንያት አለኝ:: ባሳለፍነው ሳምንት እሁድ ማለትም ከትላንት በስቲያ ከቤት ወጥቼ ወደ ብሔራዊ ቲያትር አካባቢ የሄድኩት ከቀኑ 6 ሰዓት ነበር:: ታክሲ ውስጥ እያለሁ ዝናብ መዝነብ ጀመረ:: ከፒያሳ ተነስቼ የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ሕንፃ ስደርስ የሚወርደውን ዶፍ ዝናብ ዝናብ ብሎ ለመጥራት ያዳግታል::

ይህን አጋጣሚ በመጠቀም የተሳፈርኩበት ታክሲ ሰዎችን ከአቅሙ በላይ እንደሰርዲን ጠቅጥቋል:: ምንም እንኳን አብዛኛው ተሳፋሪ መውረድ የሚፈልገው ብሔራዊ ቴአትር በር ላይ ቢሆንም አልተቻለም:: አንደኛ፣ ያ ሁሉ የዝናብ መዓት እየወረደ ማንም ከታክሲው ለመውረድ ፈቃደኛ አልሆነም:: ዋናውና ሁለተኛው ነገር ግን ከብሔራዊ ቴአትር በር እስከ ለገሃር የትራፊክ መብራት ጫፍ ድረስ በግምት እስከ ጉልበት ድረስ የሚውጥ ጐርፍ አካባቢውን አጥለቅልቆታል:: የጐርፉ ሀይልና ግስጋሴ ማንንም እኔ ነኝ ያለ ጉልበተኛ አንገዳግዶ ከመጣል አይመለስም:: በዚህ መሀል እኔ ያለሁበት ታክሲ ተሳፋሪዎች፣ «ከብሔራዊ ቴአትር አልፈህ አውርደን» ቢሉም ወደፊት እየሄደ በመጣ ቁጥር የጐርፉ መጠን እየጨመረ መጣ:: በረዶውም ለጉድ ይወርዳል:: በዚህ መሃል ብዙ ታክሲዎች ሞተራቸው ውስጥ ውሃ እየገባ ቀጥ ብለው ቆሙ:: በግምት ከ40 ደቂቃ በላይ ተበላሽቶ በቆመው ማለትም በተሳፈርንበት ታክሲ ውስጥ ተቀመጥን:: ዝናቡ ጋብ እንዳለ ከታክሲው ስንወርድ ሰው ከዋናው አስፋልት ወደብሔራዊ ቴአትር ለመሻገር በግድ መታዘል ያስፈልግ ነበር:: አንድ ሰው አዝሎ

ለማሻገር አንድ ብር የሚያስከፍሉት ወጣቶች ለጊዜው ለራሳቸው ስራ ፈጥረዋል:: ሆኖም በየመንገዱ ለዚሁ ተግባር የተሰሩት ቱቦዎች ለመሆኑ ምን እክል ገጠማቸው ሊባል ነው? መቼም ይህ ጉዳይ የሚመለከተው አካል ዝናብ ከመምጣቱ ማለትም ክረምት ከመግባቱ በፊት ቱቦዎቹ ፀድተው እና ተስተካክለው ሊቀመጡ እንደሚገባ ያጣዋል አንልም:: እርግጥ በየአካባቢው እና በየመንገዱ እጅግ በርካታ የጽዳት ሰራተኞች እናያለን:: ታዲያ ቱቦው ተደፍኖ እንኳን ለሰው ለተሽከርካሪ የሚያዳግት ጐርፍ ከተማዋን ሲያጥለቀልቃት የህዝቡን ችግር የሚረዳለት ማነው? ይህ በእውነቱ እጅግ አሳዛኝ ነገር ነው:: እና አስቸኳይ እልባት ሊበጅለት ይገባልና የሚመለከተው አካል መፍትሄ ቢፈልግለት እላለሁ::

*መግለጫ*

# የአንድነት ስራ አስፈፃሚ በስልጣን መባለግ

## ክፍል ሁለት

## ለአንድነት አባላት በሙሉ

ውድ አባላት! ፓርቲያችን አንድነት ብዙዎች የታሰሩለት፣ የተንገላቱለትና ደማቸውን አፍስሰው መስዋዕት የሆኑለት የቅንጅት ዓላማ በኢህአዴግ አምባገነናዊ አገዛዝና በራሱ በቅንጅት የውስጥ ችግሮች ምክንያት ሊጠፋ በተቃረበበት ጊዜ ፈጥኖ በመድረስ ለኢትዮጵያ ህዝብ የተስፋ ጭላንጭል ማሳየት ችሎ ነበር::

ዛሬ ግን የትናንት ቁስላችን በቅጡ ሳይሽር ያኔ በቅንጅት ውስጥ የነበረው ኢ-ዴሞክራሲያዊ አሰራርና ግለሰባዊ ፈላጭ ቆራጭነት በአንድነት ውስጥም በመንሰራፋቱ የታየው የተስፋ ጭላንጭል ሊጠፋ ተቃርቧል::

ይህ ሁኔታ ያሰጋን «የአንድነት መርህ ይከበር» የምንል የፓርቲው አባላት ችግሮቹን ለማስወገድ የተለያዩ ጥረቶችን ስናደርግ ቆይተናል:: በተለየዩ የፖለቲካው መዋቅሮች እስከ ብሔራዊ ም/ቤት ድረስ ለሚገኙ አካላት ጉዳዩን በተለያየ መንገድ ከማሳሰባችንም በላይ ከፓርቲው ተቆርቋሪ አባላት በሚል አንድ የመወያያ ጽሁፍ ለብሔራዊ ም/ቤት አቅርበናል:: ይህንን ተግባር ብሔራዊ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው በበጎ ተመልክቶ ለተጠቀሱት ችግሮች መፍትሄ ከመፈለግ ይልቅ በባሰ ሁኔታ ቀጥሎበታል:: በዚህ ምክንያት ችግሮችን ሁሉ የጉዳዩ ባለቤት ለሆኑት የፓርቲው አባላት «የአንድነት ሥራ አስፈፃሚው በስልጣን መባለግ» በሚል ርዕስ ችግሮችን የሚጠቁም ጽሁፍ ሐምሌ 5 ቀን 2001 ዓ.ም አቅርበናል:: ይህን ጽሁፍ ተከትሎ ብሔራዊ የሥራ አስፈፃሚ

ኮሚቴው የተጠቀሱትን የፓርቲውን ችግሮች ለማስተካከል የመፍትሄ እርምጃ ከመወሰድ ይልቅ በለመደው የጡንቻ አሰራር ቀጥሎበታል፡፡ እኛ ባቀረብነው ጽሁፍ ላይ ስለመለየት ያነሳነው ነገር የለም፡፡ ነገር ግን የፓርቲው ቃል አቀባይ ዶ/ር ኃይሉ አርአያ በተደጋጋሚ ልዩነታችን የመድረክ ጉዳይ እንደሆነ ሲገልፁ አድምጠናል፡፡ ከዚያ በኋላ በወጡ መግለጫዎችም ላይ ይሄንኑ ሃሳብ «የመድረክ ጉዳይ የሚሰነፍጣቸው» በሚል በሚሰነፍጥ አገላለጽ አስቀምጠውታል፡፡ እርግጥ ነው ልዩነት አለን፡፡ የልዩነታችን መሠረት ግን የመድረክ ጉዳይ ፈጽሞ ሊሆን አይችልም፡፡ እኛ ለአንድነት የምንቆረቆር የአንድነት አባላት ነን፣ ጉዳያችንም አንድነትና አንድነት ብቻ ነው፡፡ ታዲያ በኛና በብሔራዊ የስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው መሀከል ያለው ልዩነት እንዴትና መቼ ተፈጠረ?

## ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ --- የልዩነቶች ሁሉ መነሻ

ፍፁም ዴሞክራሲያዊ በሆነ ምርጫ በከፍተኛ የድምጽ ልዩነት ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ የፓርቲያችን ሊቀመንበር ሆና በመመረጧ ተበሳጭተው «እንዴት እኔ ሊቀመንበር አልሆንኩም» በሚል ያልተገባ አስተሳሰብ ለሦስት ወራት አኩርፈው ቤታቸው የተቀመጡት ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው በስንት ልመናና ሽምግልና ወደ ፓርቲው ሊመለሱ መቻላቸውን ሁላችሁም የምታወቁት ሀቅ ስለሆነ አስታዋሽ አያሻችሁም፡፡

ዶ/ር ያዕቆብ ኃ/ማርያም ምስክር ባለበት አንዴ «ልጅ አትመራኝም» ሌላ ጊዜ «ሴት አትመራኝም» ሲሉ ከመደመጣቸውም በላይ የእነዚህን ግለሰቦች ሀሳብ የሚደግፉ አንዳንድ አባላትም ፓርቲውን ሲንጡትና ሲያምሱት ከርመዋል፡፡ ሁሉም ነገር የፓርቲያችንን ገመና ሰው አይስማው በሚል እሳቤ ተሸፍኖ በሽምግልና፣ በልመናም፣ በመደለያም አንድነት ጉዞውን ቀጠለ፡፡

ከዚህም በላይ ኢህአዴግ መሪያችን ወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳን ለማሰር ሲያኮበኩብና ቀን እየቆረጠ ለማስፈራራት ሲሞክር ብሔራዊ የስራ አስፈጻሚው ኮሚቴው በ12 ድጋፍ በ1 ተቃውሞና በ1 ተአቅቦ ያሳለፈው ውሳኔ መሪያችንን ለኢህአዴግ አሳልፎ የሰጠ የማይዘነጋ ታሪካዊ ክስተት ነው፡፡ ይህ መልካም አጋጣሚ የተቸረው ኢህአዴግም መሪያችን ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳን አስሮ በጨለማ ቤት ውስጥ ከረቸመባት፡፡ እዚህ ላይ ነው እንግዲህ የልዩነታችን ዋናው መነሻ የሆነ ተግባር ለመፈፀም የተገደድነው፡፡

የብሔራዊ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ውሳኔ ያሳዘነን አባላት ተሰብስበን ውሳኔውን መልሶ ማጤን እንዲችል ደብዳቤ በመፃፋችን፣ ከመላው የፓርቲው አባላት ጋር በመሆን የወ/ት ብርቱካን ሚደቅሳ እስር ከረፈደም ቢሆን የፓርቲው ጉዳይ እንዲሆን በማድረጋችን፣ የብ/ም/ቤቱን አባላት ፒቲሽን አስፈርመን ስብሰባ በማስጠራታችንና «ዛሬም ነገም መሪያችን ወ/ት ብርቱካን ናት» የሚል ወሳኔ በም/ቤቱ በመወሰኑ ቅር የተሰኙ አመራሮች እስከ ዛሬ በክፉ ሲያዩን ቆይተዋል፡፡

ዶ/ር ሃይሉ አርአያ በአውራምባ ታይምስ ጋዜጣ፣ የተከበሩ አቶ እንዳልካቸው ሞላ በጎግል ጋዜጣ ላይ የወ/ት ብርቱካን እስር የራሷ ጉዳይ እንጂ የፓርቲው እንዳልሆነ

አድርገው የሰጡት መግለጫ እኛን ብቻ ሳይሆን መላውን የኢትዮጵያ ህዝብ ያሳዘነ ክስተት እንደነበር የሚታወቅ ነው:: ሌሎች በጋዜጣ አይናገሩት እንጂ በተለያዩ ስብሰባዎች ላይ የራስሽ ጉዳይ ነው ብለዋል::

በዚህ ጉዳይ ላይ በተካሄደ አንድ የም/ቤት ስብሰባ ወቅት የቀደመ ቂማቸውን ለመወጣት የሚመስል ሁኔታ ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው እንዴት በህግ መብቷ የተገፈፈን ሴት ሊቀመንበር እናደርጋለን ሲሉ ያቀረቡት ርካሽ የመከራከሪያ ሀሳብ ኢህአዴግ ከፈፀመው እስር የማይተናነስ የክህደት ተግባር መሆኑን አሳምነን ውድቅ ማስደረጋችንም የልዩነታችንን በር ያሰፋ ሁኔታ ነው::

ከዚህም ሌላ የብሔራዊ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴው ብቻዋን በጨለማ ክፍል ታስራ ስላለችው መሪው ተደጋጋሚ መግለጫ በማውጣትና ሌሎች የተቃውሞ መድረኮችን እየፈጠረ ለማስፈታት ከመጣር ይልቅ እንድትረሳና እስሯም ያበቃለት እንዲሆን ማድበስበስ ሲጀመር ሌላ ተቃውሞ ተቀሰቀሰ:: በዚህ ጊዜ ከእነሱ ጋር አተካራ ወስጥ ከመግባት የራሳችንን አስተዋጽኦ እናበርክት በማለት በወጣቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ አባላት በኩል ቃሌ የሻማ ምሽት ማዘጋጀት ስንጀምር በቃሌ ላይ የምንሳተፍና ስለ መሪያችን መረሳት ጉዳይ በተደጋጋሚ የምናነሳ ወጣቶች በስራ አስፈፃሚው በተለይም በዋና ፀሀፊው ጥርስ ውስጥ ገባን:: ዋና ፀሀፊው አቶ አስራት ጣሴም «የብርቱካንን ፎቶ እያስቀደሙ ፓርቲ ሊያፈርሱ ነው::» እያሉ በየጋዜጣው መወንጀል መደበኛ ተግባራቸው ሆነ:: ከዚህም አልፈው የብርቱካንን ስም የሚያነሱ የጽ/ቤቱ ሰራተኞችን በሰበብ አስባብ ከስራ አባረሯቸው::

ብሔራዊ ም/ቤቱ የመሪያችንን ጉዳይ የሚከታተሉ 5 ኮሚቴዎችን ቢያቋቁምም ኮሚቴዎቹ የሚመሩት የራስሽ ጉዳይ ነው ሲሉ በነበሩ ሰዎች ስለነበር አንዱም ኮሚቴ ጭራሽ የሚታይ ስራ ሳይሰራ ሁሉም እንዲከስሙ ተደርገዋል:: ስራ አስፈፃሚው ኃላፊነቱን ወስዶ በብርቱካን እስር ዙሪያ ባዘጋጀው ብቸኛው ቃሌ ሲምፖዚየም ላይ የተፈፀመውን አሳዛኝ ድርጊት ሁላችሁም ታውቁታላችሁ::

ተወደደም ተጠላም ትናንትም ዛሬም ወደፊትም መሪያችን ወ/ሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ናት:: ስራ አስፈፃሚው ስለ መሪያችን ትንፍሽ ለማለት የሚተናነቀው ቢሆንም ውጭ ሀገር ባሉ ደጋፊዎቻችን ከፍተኛ ብርታትና በእርሷ ቆራጥነት የተመላው ተግባር አለም አቀፍ ዕውቅና ስላገኘች ፈጽሞ ልትዘነጋ አለመቻሏን ኢህአዴግም ሆነ ሌሎቹ እየመረራቸው የሚውጡት ሀቅ ነው::

በመሆኑም በአንድነት ፓርቲ ውስጥ ልዩነት አለ ከተባለ ከጥንስሱ ያለሚትን ስልጣን ለመቆናጠጥ በህግም ይሁን ያለ ህግ በደንባዊ ውሳኔም ይሁን በፓለቲካዊ ውሳኔ እንገዛ በሚሉና **የለም ያለ ህግና ያለ ስርዓት ሊሆን የሚችል አንዳችም ነገር የለም፣ የአንድነት መርህ ሳይሸራረፍ መከበር አለበት** በምንል አባላት መሀከል ያለ ልዩነት ነው:: የእነዚህ ህገወጥ አካሄዶችና ፓለቲካዊ ወሳኔዎች መገለጫ የሆኑት ነጥቦች ሐምሌ 5 ቀን 2001 ዓ.ም ለአባላት ባቀረብነው ጽሁፍ ላይ ዘርዝረናቸዋል::

# ጽሁፉ ለአባላት ከቀረበ በኋላ የተወሰዱ ህገወጥ እርምጃዎች

በዕለቱ ያዘጋጀነውን ጽሁፍ ለአባላት ካደረስን በኋላ የተወሰደው የመጀመርያ እርምጃ ጽሁፉን ከአባላቱ እጅ እየነጠቁ መሰብሰብ ሲሆን የአቅራቢዎችን ስም የማጥፋት ዘመቻውም የተጀመረው የጽሁፉ ይዘት ሳይመረመር በዚያው ቅጽበት ነበር:: በማግስቱ ሰኞ ሐምሌ 6 ቀን 2001 ዓ.ም ደገመና ሶስት አባላትን ከድርጅት ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ አግደናል ተባለ:: ማክሰኞ እለትም ሃያ አንዱን አባላት እንዳገዱ የፓርቲው ቃል አቀባይ ዶ/ር ኃይሉ አርአያ በጋዜጦች ላይ አወጁ:: ይህ የማያዋጣ መሆኑ ሲታወቅ ደግሞ ብ/ም/ቤቱን ጠርተው «ጉዳዩ በዲሲፕሊን ኮሚቴ እንዲታይ ተወስኗል::» ወደሚል ቅስቀሳ ተንሸራተቱ::

የፓርቲው የዲሲፕሊን መመሪያ በአንቀጽ 7.1 ላይ «ብሔራዊ የዲሲፕሊን ኮሚቴ በህግና ስነ ሥርዓት ቋሚ ኮሚቴ የሚቋቋም ሆኖ በሥራ አስፈፃሚውና በብ/ም/ቤቱ ይጸድቃል» የሚል ቢሆንም ባልፀደቀና በማይታወቅ ኮሚቴ ጉዳዩ እንዲታይ መደረጉ ስህተት ነው:: ያም ቢሆን ይህ እነሱ ህጋዊ ነው የሚሉት ህገ ወጥ የዲሲፕሊን ኮሚቴ እንኳን ሊያሳልፍ የሚችለውን ውሳኔ ሳይጠብቁ /ምን እንደሚወስን ይታወቃል/

1. ዶ/ር ሽመልስ ተ/ፃዲቅ ከም/ቤት ሰብሳቢነታቸው እንዲነሱ ተደርጓል::
2. አቶ ወሮታው ዋሴ ከኦዲትና ቁጥጥር ኮሚሽን ሰብሳቢነታቸው እንዲነሱ ተደርጓል::
3. በአቶ የሺዋስ አሰፋ ምትክ አቶ አበባየሁ ደሜ የወጣቶች ጉዳይ ም/ሰብሳቢ ተደርገው በደብዳቤ ተሹመዋል::
4. የበርካታ ክ/ከተሞች ሰብሳቢዎችና ስ/አ ኮሚቴ አባላት የአንድነት መርህ ይከበር ከሚሉት ወገን በመሆን ስማቸውን በማስፈራቸው ፍፁም ህገወጥ በሆነ አካሄድ የየክ/ ከተሞችን ፋይል ማኖርያ ሎከር ሰብረው ቁልፍ እንዲቀየር አድርገዋል:
5. ዶ/ር ሽመልስ ተ/ፃዲቅና ወ/ሪት ሐና ዋለልኝ ከምርጫ ጉዳይ ቋማ ኮሚቴ እንዲወገዱ ተደርጓል::
6. አቶ ይልቃል ጌትነት/ አቶ አለባቸው አያሌውና አቶ እንደሻው እምሻው ከድርጅት ጉደይ ቋሚ ኮሚቴ እንዲወገዱ ተደርጓል::
7. ብሔራዊ ምክር ቤቱ የኤዲቶሪያል ቦርድ ሰብሳቢ አድርጐ የመረጣቸውና በዶ/ር ኃይሉ አቅራቢነት ስራ አስፈፃሚው የሕዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴ አባል አድርጐ የመደባቸው አቶ ደበበ እሸቱ የአንድነት መርህ ይከበር በማለታቸው ብቻ በራሳቸው በዶ/ር ኃይሉ አንደበት «የፓርቲው አባል አይደለም» የሚል ክህደት ተፈጽሞባቸዋል:: እነዚህ ሁሉ ህገወጥ ድረጊቶች ሲፈጸሙ ከአባላት ጋር ተባብሮ የህግ ያለህ ብሎ ከመጮህ ውጭ ሌላ ምን ምርጫ አለ?

ለአባላት ጽሁፍ ማቅረብ ለምን ተፈለገ?

ሐምሌ 5 ቀን 2001 ዓ.ም ለአባላት የቀረበው ጽሁፍ ሦስት ዋና ዋና መነሻ ምክንያቶች አሉት

1. ሚያዚያ 3 ቀን 2001 ዓ.ም በስራ አስፈፃሚው የአሰራር ድክመት ላይ ያተኮሩና መፍትሄ የሚሹ ነጥቦችን የያዘ ጽሁፍ ለም/ቤቱ ቀርቦ በነበረበት ወቅት ም/ቤቱም ግንቦት 8 እና 9 ቀን 2001 ዓ.ም ተወያይቶ ከ15 ቀን እስከ 2 ወር ድረስ ባለ ጊዜ ሊፈፀሙ ይገባቸዋል ብሎ ካሳለፋቸው 22 ውሳኔዎች ውስጥ ከመድረክ ጉዳይ በስተቀር ተፈፃሚ ባለመሆናቸውና ተድበስብሰው እንዲታለፉ በመደረጉ፣ ይህን ጉዳይ በም/ቤቱ ውይይት እንዳይደረግ በአደገኛ ቡድናዊ አሰራር በመታፈኑ፣
2. በተለያዩ የፓርቲው መዋቅር ውስጥ ያለን አባላት ከስራ አስፈፃሚው ጋር ውይይት ለማድረግ ጠይቀን ፈቃደኝነት ባለመኖሩ፣ (ይህንን ለማስረዳት የሕዝብ ግንኙነት ቋሚ ኮሚቴና የጉለሌ ክ/ከተማ ስራ አስፈፃሚ ኮሚቴን ውድቅ የተደረጉ የውይይት ጥያቄዎች ለአብነት ማንሳት የሚቻል ሲሆን ሐምሌ 5 ቀን 2001 ዓ.ም ጹሁፉን ለአባላት ባቀረብንበት ዕለት በአደባባይ የውይይት ጥያቄ አቅርበን ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው በሶስት ቀን ውስጥ ውይይቱን ለማስጀመር በመላው የፓርቲያችን አባላት ፊት ቃል የገቡ ቢሆንም ከዛ ይልቅ በሶስት ቀን ውስጥ የዕገዳ እርምጃና መግለጫ ማውጣት መምረጣቸውን መግለጽ ይቻላል::)
3. ከሁሉ በላይ በፓርቲያችን ውስጥ አሉ የምንላቸውን ችግር ሁሉ አባላት ማወቅ አለባቸው ከሚል ጽኑ እምነት የመነጨ ነው:: ጹሁፉን ያቀረብነው ጊዜአቸውን፣ ገንዘባቸውንና ህይወታቸውን ለመሰዋት ቆርጠው ፓርቲያችንን የተቀላቀሉ አባላት የገፈቱ ቀማሽ፣ የጉዳዩ ባለቤት በመሆናቸው ዛሬ በሽፍንፍን ታልፎ ነገ ወደ ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ ውስጥ ከመግባታቸው በፊት ያለውን ደረቅ እውነታ አውቀው ፓርቲያቸውን በማጥራት ሂደት ውስጥ ተሳታፊ እንዲሆኑ ነው::

ውድ አባላት! ፓርቲያችን የሚገኝበት ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ በመሆኑ የመፍትሄው አካል በመሆን በንቃት ትሳተፉ ዘንድ እውነቱን ለእናንተ ለመግለጽ ተገደናል::: በፓርቲያችን ውስጥ ያሉ የመርህ ጥሰቶች እስካልታረሙ ድረስ አሁንም ወደፊትም በዚህ ተግባራችን እንገፋበታለን::

## ዝም አንበል ! የአንድነት ጉዳይ የሕዝብ ጉዳይ ነው!

# ምርጫ ሲደርስ ፖለቲከኞች ኮሜድያን ይሆናሉ

**በፍስሐ ያዜ**

ምርጫ ሲደርስ የገዢው ፓርቲና አንዳንድ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላት ሁለት የተለያዩ ገጽታዎችን ማንፀባረቅ ይጀምራሉ፡፡ የትኛው አካል ምን ዓይነት ገጽታ እንደሚያንፀባርቅ ደግሞ ከምልከታዬ ተነስቼ ትዝብቴን በሚከተለው መልኩ በማስፈር ለውድ አንባብያን ለማሳየት ሻትኩ፡፡

የገዥው ፓርቲ አባላት በዚህ በተጠቀሰው ወቅት መዳረሻ አካባቢ በየመድረኩ በብዛት እንመለከታቸዋለን፡፡ በየኮንፈረንሱ ንግግር ሲያደርጉም ከመደበኛው (ከተለመደው) አነጋገራቸው ወጣ በማለት አገላለፃቸው ሁሉ ፈገግታን የተላበሰ ይሆናል፡፡ የወደፊቱን እቅድ ባጭር ጊዜ እንደሚያሳኩ በንግግር ሳይሆን በመሻላ ቀረሽ ንግግር ይተነትናሉ፡፡ ለአራትና ለሶስት ዓመታት ትዝ ብሏቸው የማያውቀውን የሕዝብ እሮሮ በራሳቸው ጊዜ እያስታወሱ ችግሩን እንደሚቀርፉ በእርግጠኝነት ይናገራሉ፡፡

በየክልሉ እየዞሩ ይህን መሰል ውይይት ሲያደርጉም የ«ሀይ ስኩል» ቆይታችንን ተረት ያስታውሱናል፡፡ «ከዓመት ጥናት፣ ያንድ ቀን የዓይን ጥራት» የሚለውን «የሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ» አይነት ተረት ማለት ነው፡፡ ይህን አይነቱን ተረት ወደ አገራችን ፓለቲከኞችና የመንግስት ባለሥልጣናት አምጥተን፤ ከምርጫ መቃረብ ጋር ተያይዞ ስለሚደረገው የምረጡኝ ልምምጥ ጋር ስናዋህደው ግን ተረት ተረቱ ከሰርገኛ መጣ በርበሬ ቀንጥሱ ወደ ሰርገኛ መጣ ቃሪያ ትከሉ የማለት ያህል መሆኑ ይገባናል፡፡ እናም ምርጫ ሲደርስ በንግግር መሀል የተሰበሰበውን ሕዝብ የሚያስቅ (አንዳንዱን የሚያሳቅቅ) ቀልድ አዘል አነጋገሮች፣ ተረብ አዘል አገላለጾች ይበረክታሉ፡፡

ለዓመታት ታይቶ የማይታወቅን የባለሥልጣናት ጥርስና ፈገግታ ለመጀመሪያ ጊዜ የምናዬው በዚሁ በተጠቀሰው ወቅት ነው፡፡ «ለካስ እገሌም እንደሰው ይስቃል?» ብለን እስክንገረም ድረስ፡፡ ባጠቃላይ ምርጫ ሲደርስ ባለስልጣናቱ ሁሉ ኮሜዲያን ይሆናሉ፡፡

የምንመለከተው ኢትዮጵያ ውስጥ ስለተካሄደውና ስለሚካሄደው ምርጫና ምርጫን ተንተርሰው ሲከሰቱ ስለምናያቸው ነገሮች ነው፡፡ ይህን አንኳር ነጥብ ደግሞ ለአገላለጽም ለአነባበብም ያመቸን ዘንደ ነገሩን እንደ የቴአትር መድረክ እንሳለው፡፡ አሁን «ምርጫ» የሚለው ተውኔት መድረክ ላይ ሊመደረክ ነው፡፡ ታዳሚው ሕዝቡ ነው፡፡ የገዢው ፓርቲ አባላት ኮሜዲ ፓርቱን ሲተውኑ ተቃዋሚዎች ደግሞ ትራጀዲ ፓርቱን ይተውናሉ፡፡ «አቀንቃኝና ተቀናቃኝ ገጸ-ባህሪያት» ሆነው ማለት ነው፡፡ ይህ ቴአትር እንዲደገም የመጠየቅ መብት የታዳሚው ነው፡፡ በየአራትና አምስት ዓመት ልዩነት ለእይታ የሚበቃውን ቴአትር «አጽርኦተ ታሪክ» በዚህ መልኩ በምናባችን ከሳልነው ይበቃል፡፡ አስከትዬ ማን የትኛውን አይነት ክፍል (ገቢር) መርጦ እንደተወነበት መግለጽ ግድ ይለኛል፡፡

የገዢውን ፓርቲ ሁኔታ ከላይ አይተነዋልና ስለተቃዋሚ ፓርቲዎች አሳዛኝ ገጽታ መቀጠል ይቀረኛል:: በፍላጎት ይሁን ባለመተማመን፣በመፈራራት ይሁን በሌላ ምክንያት ለታዳሚው ግልጽ ያልሆነ አወዛጋቢ ቃለ-ተውኔት (dialogue) ከተቃዋሚ ፓርቲ አባላት እንደበት ይደመጣል:: ለዚህም ነው ትራጀዲ ፓርቱን የእነሱ መገለጫ ለማድረግ የተገደድኩት::

እንደተባለውም ምርጫ ሲደርስ ማን የትኛውን አይነት ገፀ-ባህሪ ተላብሶ እንደሚተውን ቀድሞ የተገለፀለት ያህል የስራ ክፍፍሉ ቋሚ ሆኖ እናየዋለን:: በዚህ ክፍፍል መሰረትም፣ ከገዥው ፓርቲ መገለጫ (ኮሜዲነት) በተቃራኒ የሆኑት ተቃዋሚ ፓርቲዎች በመሰነጣጠቅ፣ በመዘላለፍ፣ በመተማማት፣ በመተጋገድ፣ በመካካድ፤ የተለያየ ያልነበረው አቋማቸው መለያየት፣ የሹም ሽር ግጭቶች፣ የስልጣን ሹክቻዎች፣ የአንድን አባል የአቋም መግለጫ ሌላኛው ባልደረባ እንደማያምንበት መግለጽና ወዘተ ተመሳሳይ የሆኑ ነገሮች ይከሰታሉ:: (ጥቂቶች ጽኑ መሆናቸውን ሳንዘነጋ) እናም፣ ሴራው ወደ ግጭት ከግጭት ወደ ጡዘት በፍጥነት የሚያመራው ቴአትሩ ለእይታ ሊቀርብ ሲቃረብ ነው:: ትብብር፣ ቅንጅት፣ ሕብረት፣ አንድነት (የፓርቲ ስያሜዎች አይደሉም) የሚሉ ቃላቶች ይበረክታሉ::

አንዱ ካንዱ ያበረ እየመሰለ ለሒደቱ መሰናከል ስራውን ሲሰራ ሌላው በትብብሩ ተስፋ ሲጥል ቴአትሩ ታዳሚውን ያጓጓል:: አጓጉቶ አጓጉቶ አጨራረሱ ላይ ያልተጠበቀ ክስተት ይፈጠራል:: ልክ እንደ ልብ ሰቃይ የኪነ ጥበብ ዘርፍ ውጤትነቱ ማለት ነው:: ይህን ግጭትና ጡዘት መሰረት በማድረግም ገዥው ፓርቲ ጠንካራ ተዋናይ በታሪኩ እንዳላየ ደጋግሞ ከመግለፁ ባሻገርም ከትራጀዲ ፓርቱ ኮሜዲ ፓርቱን ወደ መውደድና እሱኑ ገቢር ብቻ መተወንን ይመርጣል:: ምክንያቱም በአሳዛኙ ጎራ ተሰልፈው በራሳቸው ሴራ ተጠላልፈው እራሳቸው ከጠለፉት ገመድ ራሳቸውን መፍታት ሲሳናቸው ያየው (የሚያየው) ታዲያ እነዚህን ገፀ-ባህሪያት በሴራ ተግባር ብቻ ተሰማርተው እንዲቀጥሉና በቴአትሩ ተመልካቾች ዘንድ እንዲጠሉ የማይፈነቅሉት ድንጋይ አይኖርም:: የእነሱ ብቻ ቃለ-ተወኔት እንዲደመጥ ይፈልጋሉ::

ስለዚህ ተመልካቹ በፈገግታና በሳቅ ጫዎታ በታጀበ ንግግር ብቻ ተመስጦ ቁም ነገር ሳይገበይ ቴአትሩ እንዳይጠናቀቅ ጥቆማ ያሻዋል:: ኮሜዲያኑም (የትራጀዲ ፓርቱ ተዋንያን) ከሴራቸው ወጣ ማለት ይጠበቅባቸዋል:: ታዳሚ እንዲማረርም በር መክፈት የለባቸውም:: ይህ ሁሉ ካልሆነ ታዳሚው ሁለቱንም ጠልቶ ቴአትሩን አለማየት ይመርጣል:: በዚህ ጊዜ ደግሞ ተመልካች በሌለበት ትወናው ይቀጥላል:: ይህም የብቻ ውድድር ተብሎ ሊገለጽ የሚችል ይመስለኛል:: ይመስለኛል ብቻም ሳይሆን በማሚያው አይቻለሁ፣ አይታችኋል አይተናል:: በሌላ አገላለጽ ኮሜዲያኖቹ ኮሜዲ ፓርቱን ብቻ የተወኑበት አጋጣሚ ተፈጥሯል::

ይህ ሊሆን የቻለውም «መድረኩን ተመልካች አልባ ያደረጉት ኮሜዲ ፓርቱን የሚጫወቱት ሳይሆኑ ትራጀዲ ፓርቱን የሚወክሉት ተዋንያን ወደ መድረኩ ስላልመጡ

ነው» በማለት ኮሜዲያኑ ያምናሉ፣ ያሳምናሉ፡፡ (የራሳቸውን ግድፈት ክደው) በዚህ መልክ ታዳሚውም ተዋንያኑም፣ ቴአትሩም፣ መድረኩም ቅጥ ያጣሉ፡፡ ያልተጠበቀው አጨራረስም ተደጋግሞ ይከሰታል፡፡

በዚህ ምሳሌያዊ አገላለጽ የአገራችን የፖለቲካ ሒደት ለማሳየት የዳዳሁትም ካለፈውና አሁን ከማየው በመነሳት ነው፡፡ በዚያ ላይ እንደ ታዳሚነቴ ስለተውኔቱ ምላሽ (feedback) መስጠት ይጠበቅብኛልና ነው፡፡

የገዥው ፓርቲ አባላት በፍልቅልቅታ የተሞላ ውይይታቸውን፣ ቀልድና ተረብ አዘል አገላለፃቸውን (አተዋወናቸውን) ተመልክቶ ኮሜድያን ብላቸው፣ የተቃዋሚ ፓርቲ አባላትን መከዳዳት፣ መቧጨቅና መሰነጣጠቅ ተመልክቼ ትራጄዲ ብላቸው ማን ሊቃወመኝ ይችላል?!!!

# እርስ በርሷ የምትለያይ መንግስት አትፀናም!

**በመርዓዊ ሜጌሶ**

**(ሕግ አውጪ + ሕግ አስፈፃሚ + ሕግ ተርጓሚ) ➔ የመንግስት ፅናት**

**(ሕግ አውጪ ≠ ሕግ አስፈፃሚ ≠ ሕግ ተርጓሚ) ➔ የመንግስት ውድቀት**

አሜሪካዊ ፀሐፊና የፍልስፍና ሰው ኤመርሰን የመርሆን ታላቅነት አስመልክቶ « መርሆዎችን ብታውቅ ልዩ ልዩ አሰራሮች ልትነድፍ የምትችል ሲሆን፣ አሰራሮች/አደራረጎች (methods) ብቻ ብትማር ግን በአሰራሮች ትቀፈደዳለህ» ሲል የመርሆን ታላቅነት የገለጸ ሲሆን፣ «ከመርሆ ተነስተህ ስትሰራ አካሄድህ አስተማማኝ ይሆናል፤ ከአሰራር ስትነሳ ግን ሌላ ምንዛሬ አይኖርህምና የአሰራር ቁራኛ ትሆናለህ» በማለት አስተምሯል፡፡

በዚህ ፅሁፍ ርዕስ የተገለጸው አባባል ለዘመናት ሲሰራ የኖረና ወደፊትም የሚቀጥል አስተማማኝ መርህ ሲሆን፣ መርሆውን ያወቁና ያስተዋሉ አንድ አካል እርስበርስ ሲተባበርና ሲስማማ ብቻ ጤናማ ውጤት እንደሚገኝ አረጋግጠዋል፡፡

ይህን በርዕሱ የተጠቀሰውን መርህ የተናገረው የሰው ልጆችን ከዲያቢሎስና ከአለማወቅ ባርነት ወደጊዜያዊም (time) ሆነ ዘላለማዊ ነፃነት የማሻገር ተልዕኮ ይዞ የመጣው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው፡፡ እርስበርሷ የምትለያይ መንግስት እንደማትፀና የተናገረው በዚሁ የነፃ ማውጣት ተልዕኮው ላይ እያለ አንድ ጋኔን ያደረበትን ዲዳ ሰው በፈወሰ ጊዜ ነበር፡፡ ዲዳው ሲናገር የተበሳጩ ፈሪሣውያን በብኤልዜቡል (በአጋንንት

አለቃ) አጋንንት ያወጣል በማለት ሲናገሩት፣ መንግስት እርስበርሷ ከተለያየች ያቺ መንግስት እንዴት ትቆማለች? እኔ በአጋንንት አለቃ አጋንንት ካወጣሁ የአጋንንት መንግስት እንዴት ይቆማል? በማለት እውርነታቸውንና ድንቁርናቸውን ነቅፎ በመገሰጽ የተናገረው መርሆ ነው - ይህ ከላይ የተገለፀው መርህ:: ሰይጣን ራሱን ተቃውሞ ከተለያየ መጨረሻ ይሆንበታል እንጂ ሊቆም አይችልም በሚል ይኸንን የዘመናት የመርሆ የማዕዘን ድንጋይ አስቀመጠ::

ይህ መርህ በማንኛውም ህብረት ላይ የሚሰራ መርህ ነው:: ለምሳሌ አንድ ቤተሰብ ወይም ትዳር የሚመራባቸው መርሆዎች ሳይከበሩ ሲቀሩ ያ ቤተሰብ ወይም ትዳር ይፈርሳል:: ለአንድ ዓላማ የሚሰሩ ህብረቶች ከመካከላቸው በዓላማው ላይ ጦር የሚወረውሩ ቢነሱበት ያ ዓላማ ፈራሽ ነው::

የሰውን መንግስት (የህዝብ አስተዳደርን) ከዚሁ መርህ አንፃር ዛሬ ብንመለከት ብዬ የተረዳሁትን ልገልፅላችሁ ፈልግያለሁ::

በነገራችን ላይ ዲሞክራሲ ያሻውን ይበል፣ የሰው መንግስት በምድር የእግዚአብሔር እንደራሴ ነውና መንግስትነት በሰው ወይም በጋኔን የሚቋቋም አይደለም (ሮሜ 13 መልእክት ይነበብ)::

አምላክ ዲሞክራሲ፣ መንግስት በህዝብ ፈቃድ ይቋቋማል በማለት ሥልጣን ከህዝብ ይገኛል ባይ ነው:: ዲሞክራሲን በአምላክነት የሚሰግዱለትና የሚያጥኑለት ለዚሁ እስከመሰዋት ደርሰው የሰማዕትነት መታሰቢያ ያቆመለታል:: በዚሁ እናምናለን የሚሉት፣ በተለይም አፍቃሬ ዲሞክራሲ ምዕራባዊ አገራት በመንግስት አመራር ላይ ለመቀመጥ እኔን ሥልጣን ስጠኝ በሚል መራጩን ህዝብ በተስፋ ያማልላሉ:: በመጨረሽም ህዝቡ መረጠ ሲባል ሥልጣን ላይ ወጡ ይባላል:: የሚያስቀው ነገር ግን ዲሞክራሲ አንድ ያላየው ነገር መኖሩ ነው:: ይኸውም ምንድነው፣ ተወዳዳሪው ተመራጭ በቅድሚያ በእግዚአብሔር መመረጡን አለማስተዋሉና ህዝቡ ራሱ በማይገባው መንፈሳዊ ኃይል መነዳቱን አለማስተዋሉ ነው:: ምን ለማለት ነው፣ በተወዳዳሪውና በህዝብ ፍላጐት ጀርባ መለኰታዊ አሰራር መኖሩን ዲሞክራሲ ማሰብም አይፈልግም:: ምን አሳጣኝ ብሎ ከዚያ ውስጥ ይግባ? ግን ይህን አንድ ነገር ልብ ይሏል - ዲሞክራሲ ገባውም አልገባው በማንኛውም መንግስት አሰያየም ጀርባ የመለኰት ውሳኔ አለ:: መለኰት መስራት አለመሥራቱን ማወቅ አለማወቅህ፣ ወይም ምናልባት በዚህ አባባል በተላላነት መሳለቅህ እግዚአብሔርን ከመሥራት የሚከለክለው አይሆንም:: የምድሩና በውስጧ ያሉት ባለቤትና የበላይ አዛዥ እግዚአብሔር አምላክ ሆኖ እኔ ወይ እኛ መንግስት ወይም ንጉስ እንሾማለን ብትል የሚሳካ ይመስልሃል? «ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፣ ባለስልጣናት በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው» የሚለውን አለማመን ይጐዳል፤ ማመን ግን ይጠቅማል::

በተመራጩና በህዝቡ ጀርባ መለኰታዊ ክንድ አለ ካልክ በምርጫ መጭበርበርና በመሳሰለው ሥልጣን ሲቀማሙስ እንዴት ይገለፃል? በማለት የሚጠይቁ እንዳሉ ዕሙን

ነው:: ምርጫ ተጭበረበረ ሲባል መጭበርበሩን የማስረዳት ሸክም የማነው? ተጭበርብሮብኛል የሚለው ወገን አይደለም ወይ? ነው እንጂ! መልካም:: እሱ አቤቱታውን አቅርቦ በጉዳዩ ላይ ዳኝነት የሚሰጠው አካል አልተጭበረበረም ካለስ? ችግሩ ዳኝነቱ አይደለም እንዴ? ዳኝነቱ መብታችንን ቢያሳጣንስ? መባሉ ደግሞ አይቀርም::

በበኩሌ ለዚህ ለኋለኛው ጥያቄ አንድ መልስ ነው ያለኝ:: ይኸውም ምንድነው፣ «አህያህ ከእጅህ በኃይል ይወሰዳል ወዳንተም አይመለስም» የሚለው ርግማን ሰርቶብህ ነው የሚል ነው:: ምን ማለትህ ነው አብራራው የሚል ቀጣይ ጥያቄ ይኖራል፤ ግድ ነው:: የአባባሉን ትርጓሜ ከማየታችን በፊት ይህ ቃል የት እንደተጠቀሰ እንይ:: ቃሉ በኦሪት ዘዳግም ምዕራፍ 28 ቁጥር 31 ላይ የተፃፈ ሲሆን ይህ ቃል እግዚአብሔርን ባለማምለክና ለርሱ ብቻ ባለመገዛት ምክንያት ከተደነገጉ ቁጣዎች መካከል የሚገኝ ነው::

የድንጋጌው ባለቤት የቃሉን ፍቺ እንደገለጸልን ከሆነ አህያ የመብት ወይም የጥቅም ምሳሌ ሲሆን በርግማን ምክንያት መብት አሳይቶህ መብትህን በግላጭ የማሳጣት አፈጻጸም ሊያልፍ እንደሚችል የሚገልጽ ነው:: በምርጫ የመንግስትነት ሥልጣን አግኝቼ ነበር ተቀማሁ ካልክ መለኮት ተሳስተሃል አይልህም:: ትክክል ነህ ተቀምተህ ነው፣ የተቀማኸው ግን ከመለኮት ጋር ባለህ ጠብ ምክንያት ነው የሚልህ ይመስለኛል:: ጠቡ ከአንተ ወይንም ከደጋፊዎችህ ጋር ሊሆን ይችላል::

ስለዚህ በአንድ ምርጫ ላይ መብትህ ይፀና ዘንድ ከፈጣሪ አምላክ ጋር መስማማት ግዴታ ነው ማለት ነው:: ሥልጣን በሰው የማይመጣውን ወይም ከሰው የማይገኘውን ያህል ሥልጣን ከአጋንንቶች መንግስትም የሚገኝ አይደለም:: ለዚህም ሮሜ 13 እና ለሎችም ዋቢዎች መጥቀስ የሚቻል ሲሆን፣ በአንፃሩ ሥልጣን ከአጋንንት ዓለም ለመገኘቱ አንዳችም ጠቋሚ ማስረጃ የለም:: እዚህ ላይ ግን አንድ ነገር ልብ ይሏል፤ ነገሥታት በእግዚአብሔር የሚነግሱ ሆኖ ሳለ በሥልጣን ዘመናቸው ግን ወደመናፍስት ጠሪዎችና ጠንቋዮች በመሄድ አምላካችንን ሊበድሉ መቻላቸው ነው:: ለምሳሌ በእስራኤል የመንግስት አስተዳደር የይሁዳ ንጉስ ምናሴ መናፍስት ጠሪና ሞራ ገላጭ ሆኖ አምላክን አሳዝኖ በመጨረሻም በጽኑ ቅጣት አልፏል::

እንግዲህ ሥልጣን ከእግዚአብሔር መገኘቱን እንዲህ ባጭሩ ካረጋገጥን ዘንዳ ሥልጣን ሊሰጠን ወይም ሊነሳን ወደሚችለው አምላክ ፊታችንን እናዙር እንጂ መራጩን ህዝብ ከጉናችን ለማቆም ብዙ ባንወዛወዝ ጥሩ ነው::

የሥልጣንን ባለቤት እንደዚህ ከገለጽን በኋላ ወደተነሳንበት ወደተመራጩ መንግስት የሥልጣን ጸንቶ መቀጠል ርዕሰ ጉዳይ እናቅና:: አንድ መንግስት የሚቋቋምባቸው ዋናዎቹ አምዶች 3 ናቸው:: እነዚህም ሕግ አውጪ፣ ሕግ ተርጓሚና ሕግ አስፈፃሚ ናቸው:: እነዚህ ምሰሶዎች ሲቆሙ ቤቱም ይቆማል:: ከነዚህ ምሰሶዎች አንዱ ቢናጋና ቢፈርስ ቤቱ አይቆምም፣ ይፈርሳል እንጂ:: ስለዚህ እነዚህ ሦስቱ ከተደማመጡና በጋራ ከሠሩ ያ መንግስት (ያ መንግስታዊ ቤት) ይቀጥላል::

የሥራ ድርሻቸውን ስናስተውልም ሕግ አውጪው ዋና ሥራው መንግስቱ የሚሰራበትን የመፍትሔ ሕጎች መቀመር ነው:: ሕግ አስፈጻሚው ደግሞ ለመንግስቱ ሥራ  የሚያስፈልጉ ሕጎች ይፀድቁ ዘንድ ለሕግ አውጪው ከመምራት ጋር ራሱ መርቶ የፀደቀለትን ወይም ተቀባይነት ያላቸውን ሕጎች ይተገብር ዘንድ ይጠበቅበታል:: ሕጉ የሚሰራበትን ጥሬ እቃ (Recipe) ለፓርላማ አቅርቦ የሕጉ ኬክ በፓርላማ ተቀናብሮ ተጋግሮ ሲቀርብለት በኬኩ ባይጠቀም አስፈጻሚው ጤነኛ አይደለም እንዴ? ማለት ብቻ ነው የሚቻለው::

ሕግ ተርጓሚው በበኩሉም ፓርላማው መፍትሔ ናቸው በሚል ለልዩ ልዩ ጉዳዮች የቀመረውን የሕግ መፈወሻ (prescription) ሥራ ላይ ማዋል ሲሆን ሥራው መፍትሔውን ወደጎን ትቶ ፍትህ ቢያበላሽ የመንግስቱን አንድ አውታር እንዲወድቅ እየተጋ ነውና ያ መንግስት አይፀናም:: ፓርላማው ይኼንን ጉዳይ በዚህ ሕግ፣ ይኼንን ደግሞ በዚያኛው ፍቱልኝ እያለ የዳኝነቱ ሥርዓት ግን አንተ ባልከው ሕግ አንፈታም ቢለው ያ መንግስት ቤቱ እየፈረሰ ነውና አይፀናም::  መንግስት እርስበርሱ ተለያየ የማለት መሰረተ ሀሳብ ይኼ ነው:: ስለዚህ የሕግ የበላይነት በመሰረቱ በቅድሚያ የሚጠቅመውም ሆነ የሚጐዳው ሕጉን ያቋቋመውን መንግስት ነው::

በመሆኑም ሕጉ የበላይ ይሁን ብሎ መጨነቅ ያለበት በመሰረቱ የመንግስቱ አስተዳደር እንጂ ህዝቡ፣ ተቃዋሚው ወይም ጋዜጠኛው አይደለም በዋናነት ይሄን ማለት የሚጠበቅበት:: አንድ መንግስት ተቃዋሚ ከሚጥለው በላይ በራሱ ላይ መነሳቱ ያፈርሰዋል:: ለማንም መንግስት ተቃዋሚ ቀዳሚ ሥጋት አይደለም:: ለማንም መንግስት ቀዳሚው ሥጋት በተለይ የፍትህ አካሉ እና አስፈፃሚው ናቸው::

ማንም መንግስት በሕግ ሥርዓት ያልተገኙ ጥቅሞችን ሲያፀድቅ ሳሩን አይቶ ገደሉን ግን አላየም:: ሣሩ ጥቅሙ ሲሆን ገደሉ ግን የፓርላማን የሕግ መፍትሔነት ሥርዓት ማፍረስ ነው:: በሕግ ሥርዓት የሚገኙ መብቶችን ሲከለክልም ልክ እንደዚሁ ነው:: በሕግ ሥርዓት ሊዳኝ ተቀምጦ ያለሕግ ከፈረደ በዚህ ሂደት የመንግስቱ ሥርዓት የውስጥ መሰንጠቅ ፣ መሸርሸርና በመጨረሻም መውደቅ ይመጣበታል::

መንግስት የሕግ መከበር «ዋና ዳይሬክተር» ሆኖ ሳለ፣ ህዝብ በሕግ አምላክ እስኪለው ከጠበቀ ያ መንግሰት በመታለል ውስጥ መገኘቱን ሊያስተውል ይገባል:: ህዝቡ እየጠየቀና እየተማፀነ ያለው ሕጉ ይከበርልን እያለ ከሆነ ሕዝቡ ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለመንግስቱም ሕልውና እየሰራ ነው::

ለምሳሌ መኪናን የወሰድን እንደሆነ መኪና ለመንዳት ወይም ማሽንን አምራች ለማድረግ አግባብ ያላቸውን ቁልፎች (keys) መጫን እንጂ ቁልፎቹን ማበላሸት ውጤት አያመጣም:: መኪናውም አይጓዝም ማሽኑም አያመርትም:: መንግስትም የሕጉን ቁልፍ ከመጫን ይልቅ መሰበሩን ካስተዋለ ቤቱን እያፈረሰ እንዳለ ሊገባው ይገባል::

በመንግስት ሥርዓት መካከለኛውና ትልቁ አውታር ሕግ አውጪው ነው:: ሕግ ተርጓሚውም ሆነ ሕግ አስፈፃሚው የሕግ አውጪው ውላጆች (ልጆች) ናቸው:: ሕግ

አውጪው ልጆቹን የወለደው በዓላማ እንጂ ቤቱን በማፍረስ እንዲተጉላት አይደለም:: ልጆቹ አባታቸውን ቢያከብሩ ያ ቤት እስከሽምግልናና እስከሽበት ይቆያል:: ሁለቱንም አካላት አንተ እንደዚህ ብለህ ፈጽምልኝ! አንተኛውም እንደዚህ ብለህ ተርጉምልኝ! የሚለው ሕግ አውጭው ነው:: የአባታቸውን የመፍትሔ ሥርዓት አለመቀበል ጅል አባት ነው ያለን አንቀበለውም የማለት ያህል ነው:: ይህንን ጉዳይ በሰላም መንገድ የሚረዱት አሉ:: ስለዚህ የልጆች እድሜ የሚረዝመው ወላጆቻቸውን ሲያከብሩ ነውና በተለይ ሕግ አስፈፃሚና ሕግ ተርጓሚ አባታቸውን አክብረው ካልሰሩ ቤቱ ይፈርሳል:: በሉ እንግዲህ የገባኝን ያህል ከገባችሁ ለኔ በቂዬ ነውና ደህና ቆዩልኝ::

# «ብሔራዊ መግባት መፈጠር አለበት የሚባለው በራሱ ምክንያት የምንደግፈው አጀንዳ ነው»

**ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ**

**በግርማ ካሳ**

> **«የሰላም መንገድ ከጦርነት ይሻላል:: ይሄን የምለው እንደ አንድ ወታደር ነው:: መከላከያ ሚኒስቴር ሆኜ የእስራኤል ወታደሮች ቤተሰቦች ስቃይ ይሰማኛል:: ስነርሱ፣ ስልጆቻችን፣ ስልጅ ልጆቻችን ስንል መንግስታችን ዘላቂ ሰላም እንዲገኝ ማንኛውንም ቀዳዳ፣ ማንኛውንም እድል መጠቀም አለበት:: ሰላም አንድ ጸሎት ብቻ አይደለም:: ሰላም የጸሎታችን መጀመሪያ ነው::»**
>
> **ኢሳቅ ራቢን ከመገደላቸው በፊት የተናገሩት**

የአስራ ሰባት ዓመት ወጣት ነው:: ጥይት የጎረሰ ሽጉጥ በእጁ ይዟል:: እጅግ በጣም ብዙ ሕዝብ በተሰበሰበበት አደባባይ ንግግር አድርገው ወደ ጨረሱ አንድ የእድሜ ባለጸጋ ሰው ቀስ በቀስ ይጠጋል፤ ሳያስቡት የያዘውን ሽጉጥ ወደ እርሳቸው ደቅኖ ይተኩሳል:: ሰውዬው ይወድቃሉ:: አካባቢው ተረበሸ:: ተናወጠ:: አምቡላንስ ተጠርቶ በአፋጣኝ በስፍራው ደረሰ:: የወደቁትን አባት በአምቡላንሱ የነበሩ የህክምና ባለሞያዎች አነሷቸው:: በፍጥነት ጉዞ ወደ ሆስፒታል ጀመሩ:: ሆስፒታል ሳይደርሱ በመንገድ ላይ የእኝህ ሰው ሕይወት አለፈች::

ይህ ወጣት ይጋል አሚር ይባላል:: ተኩሶ የገደላቸውም ሰው የቀድሞ የእስራኤል ጠቅላይ ሚኒስትር ኢሳቅ ራቢን ነበሩ::

ኢሳቅ ራቢን እድሜ ዘመናቸውን በሙሉ የጥይትና የመድፍ ድምጽ በመስማት ያሳለፉ ጦረኛ ወታደር ነበሩ:: በፈረንጆች አቆጣጠር በ1941 ከታዋቂው ሞሼ ዳያን ጋር የፓልማክ ግብረኃይል አባል ሆነው፣ ያኔ በፈረንሳዮች ቅኝ ግዛት ስር በነበረችው በሊባኖስ፣ የናዚ ጀርመን ደጋፊ የነበረው የፈረንሳይ ቪቺ መንግስት ወታደሮች ጋር ተዋግተዋል:: በዚያ ጦርነት ጊዜ ነበር ሞሼ ዳያን አንድ አይናቸውን ያጡት::

ከዚያ በኋላ ከአረቦች ጋር በተደረጉት ተከታታይ ጦርነቶች ትልቅ ጀግነነትና የውትድርና ብቃት ያሳዩ፣ በእሥራኤል ታሪክ አሉ ይባሉ ከነበሩት ታላላቅ የጦር መሪዎች አንዱ ነበሩ - ኢሳቅ ራቢን:: የእሥራኤል የመከላከያ ሚኒስቴር፣ የጦሩ የኢታ ማጆር ሹም ሆነውም አገልግለዋል::

ኢሳቅ ራቢን፣ «እኔ ሰላም ሳላይ እድሜዬን ጨርሻለሁ:: ለልጆቻችን ሰላም ማምጣት አለብን::» በሚል እምነት፣ ድፍረት የተሞላበት የሰላም እርምጃ ወሰዱ - የእሥራኤል ጠላቶች ከሚባሉ ጋር መነጋገር በመጀመር::

ኢሳቅ ራቢን ከመገደላቸው ከጥቂት ደቂቃዎች በፊት የተናገሩት ለእኛ ለኢትዮጵያውያንና ለመሪዎቻችን ትልቅ ትምህርት የሚሰጥ አስደናቂ አባባል ነበር፤ «የሰላም መንገድ ከጦርነት ይሻላል:: ይሄን የምለው እንደ አንድ ወታደር ነው:: መከላከያ ሚኒስቴር ሆኜ የእስራኤል ወታደሮች ቤተሰቦች ስቃይ ይሰማኛል:: ለነርሱ፣ ለልጆቻችን፣ ለልጅ ልጆቻችን ስንል መንግስታችን ዘላቂ ሰላም እንዲገኝ ማንኛውንም ቀዳዳ፣ ማንኛውንም እድል መጠቀም አለበት:: ሰላም አንድ ጸሎት ብቻ አይደለም:: ሰላም የጸሎታችን መጀመሪያ ነው::» ነበር ያሉት::

የጦርነትን፣ የጥላቻና የእልህ ፓለቲካ አደገኛነቱን ያውቁታልና፣ አብረዋቸው የነበሩ ጓደኞቻቸው ሲረግፉ፣ አካለ ስንኩል ሲሆኑ፣ ንብረት ሲወድም፣ ሰው በሰው ላይ ሲጨክንና አውሬ ሲሆን አይተዋልና፣ እርሳቸው የኖሩበትን በጦርነት የተበከለን አየር ለልጅ ልጆቻቸው ማውረስ አልፈለጉም:: እርሳቸው ይመኙትና ይናፍቁት የነበረውን ሰላም፣ እርሳቸው ባያገኙትም እንኳን፣ የልጅ ልጆቻቸው እንዲያገኙ መደረግ ያለበትን ሁሉ ማድረግ እንዳለባቸው ተገነዘቡ:: «ለልጅ ልጆቻችን ስንል ሰላም እንዲመጣ የተገኘ ችዋን ቀዳዳ ሁሉ መጠቀም አለብን» በሚል ጽኑ እምነት፣ በጦርነት ያልሆነ፣ የውስጥና የልብ ጀግንነት ለማሳየት ተንቀሳቀሱ:: የእሥራኤል ጠላት ከተባሉት ከነያሲር አራፋት ጋር መነጋገር ጀመሩ::

ብዙ ተቃውሞ መጣባቸው:: እነናታንያሁ ተነሱባቸው:: ግትር ፖለቲካ የሚያራምዱ በጭንቅላት ሳይሆን በጠመንጃ የሚያምኑ፣ እነርሱ ብቻ ከሌላው እንደተሻሉ አድርገው በመቁጠር በትእቢት የተወጠሩ፣ ከነርሱ ዘር ውጭ ለሌላው ግድ የማይሰጣቸው ሰዎች በርሳቸው ላይ ማጉረምረም ጀመሩ::

ይሳቅ ራቢን ግን ወደ ኋላ አላሉም፤ «የሰላም ጠላቶች አሉ:: ሊጎዱን፣ የሰላሙን መንገድ ሊያጨናግፉ የሚፈልጉ:: በድፍረት እናገራለሁ:: ከፍልስጤማውያን መካከል የወጣው፣ በፊት ጠላታችን የነበረው የፍልስሰጤም ነጻ አውጭ ግንባር አሁን የሰላም

አጋራችን ሆኗል፤» ሲሉ ከቀድሞ ጠላቶቻቸው መካከል ወዳጆችን እንዳፈሩ ተናገሩ:: ከያሲር አራፋት ጋር በአንድ ላይ ለሰላም ቆሙ:: ይሳቅ ራቢን በጦርነት ሊያጠፉት ያልቻሉትን የያሲር አራፋትን ቡድን በሰላም አሸነፉት::

ታዲያ ለዘመናት በጦር ሜዳ ሲዋጉ በጥይት ያልተመቱት እኚህ ታልቅ ሰው፣ በሰላሙ ሜዳ በቴላቪብ ከተማ ጥይት አገኛቸው:: ለሰላም፣ለፍቅርና ለወንድማማችነት ሲሉ ወደቁ:: እጅግ ታሪካዊ፣ ተወዳጅ የሰላም ሰው!!!

የኢሳቅ ራቢንን ታሪክ ያለምክንያት አላመጣሁትም:: አንዳንዶቻችን ተቃዋሚዎችን መጨፍለቅ ጀግንነት ይመስለናል:: አንዳንዶቻችን ኃይልን የምንመዝነው በያዝነው ብረትና በዘረጋነው የሥለላ አውታር ነው:: መነጋገር፣ መወያየት፣ ፍቅርና መግባባት፣ በጦርነትም ሆነ በጉልበት ከሚገኝ ጊዜያዊ መፍትሔ የበለጠ ዘለቄታ ያለው ጥቅም ሊያመጣ እንደሚችል አናስብም:: የሩቁን፣ እኛ ካለፍን በኋላ በልጆቻችንና በልጅ ልጆቻችን ዘመን ሊፈጠር የሚችለውን፣ ለሁላችንም የሚበጀውን አንመለከትም:: ጊዜያዊ ጥቅማችንንና ስልጣናችን ላይ ብቻ በማተኮር ግትር ፖለቲካ እናራምዳለን::

በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በፓርላማ ተገኝተው ከተመራጮች ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡ አንዲት ቀልቤን የሳበች አባባል አደመጥኩ፤ ስለ ቀጣዩ ዓመታዊ የአገሪቷ ባጀት ነበር በፓርላማ ውይይት ሲደረግ የነበረው:: ለጦር ሰራዊቱና ለፓሊስ ከተመደበው ባጀት ተቀንሶ ወደ ሌላ ጠቃሚ ፕሮግራም እንዲውል የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ሕብረት የፓርላማ ተጠሪ አቶ ገብሩ ገብረማርያም ሀሳብ ያቀርባሉ:: የፖሊስና የደህንነት አባላትን በማብዛት ብቻ የአገር ደህንነትን ለማስጠበቅ ከመሞከር ይልቅ የችግሮች ምንጭ የሆኑትን ከሥራቸው በንግግርና በሰላም መፍታት ቢቻል የበለጠ ለአገር ጠቀሜታ ይኖረዋል በሚል «ስለ አገር በምናስብበት ጊዜ፣ ስለ እድገት በምናስብበት ጊዜ የብሔራዊ መግባባትን የመፍጠር ጉዳይ ትልቅ ትኩረት ተሰጥቶ ቢታይ ከበጀቱም ጋር ከሁሉም በላይ ጠቃሚ ነው::» ሲሉ ሃሳባቸውን ያቀርባሉ:: በሕብረቱ ተወካይ ለቀረበው ሀሳብ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ሲመልሱ፣ «ብሔራዊ መግባባት መፈጠር አለበት የሚባለው በራሱ ምክንያት የምንደግፈው አጀንዳ ነው:: የጸጥታ አስከባሪ አቅማችንን በማሽመድመድ የሚፈጠር ብሔራዊ መግባባት ግን የለም:: አገሪቱን ለውጭ ጥቃት አጋልጦ የሚፈጠር የፖለቲካ ትርፍ የለም::» አሉ::

እርግጥ ነው አገሪቱን ለውጭ ጥቃት ማጋለጥ ጸረ-ኢትዮጰያዊነት ነው:: አገሪቷ በአባይ ወንዝ አጠቃቀም ምክንያት ከግብጽ ሊነሳ የሚችልን ጥቃት፣ አል-ሻባብ በተባለው በሶማሊያ የሚንቀሳቀሰው ጨካኝ ቡድን ሊያመጣ የሚችለውን የተወሳሰበ የሽብር አደጋ በአንድነትና በጋራ እንደ ኢትዮጵያዊ መመልከት መቻል አለብን:: ሥልጣን ላይ ያለው መንግስት እኛ የምንወደው አለመሆኑ በአገራችን ላይ የመጣውን አደጋ እንዳናይ አይኖቻችን ሊሸፍነው ይችላል::

ከሰባ ዓመታት በፊት በቻይና፣ በማኦ ዜዱንግ የሚመራው የኮሚኒስት ፓርቲና በኋላ ታይዋንን በመሰረቱት በቺያንግ ካ ሼክ የሚመራዉ የ«ናሽናሊስት ፓርቲ» እርስ በርስ ይዋጉ ነበር:: ጃፓን ቻይናን በምትወርበት ጊዜ ግን እርስ በርስ ሲዋጉ የነበሩት ወገኖች በአንድነትና በጋራ የውጭ ወራሪን መመከት ጀመሩ:: እኛም ከቻይናውያን ተምረን የውስጥ ችግሮቸችን ከውጭ ችግሮቻችን መለየት መቻል አለብን እላለሁኝ::

ስለሆነም፣ የአየር ኃይላችንና የምድር ጦራችንን የበለጠ ማጠናከርና ማደራጀት ተገቢና እጅግ አስፈላጊ ነው:: የአገር አንድነት፣ የአገር ደህንነት ማንም ይግዛ ማንም ቅድሚያ ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው:: ከባጀት ጭመራውም ባለፈም መልኩ፣ ሰራዊቱ የኢትዮጵያን ሕዝብ ያንጸባረቀ፣ ከፖለቲካ ነጻ የሆነ፣ የግለሰቦችን ጥቅም ሳይሆን የአገርን ጥቅም የሚያስጠብቅ ሰራዊት እንዲሆን በተሻለ መንገድ መዋቀር ይኖርበታል:: ኢትዮጵያ ጠንካራ፣ ሁላችንም የምንኩራበትና የምንተማመንበት የመከላከያ ሰራዊት ያስፈልጋታልና:: (የውጭ ጥቃት በምልበት ጊዜ ኤርትራን እንደማልጨምር እንዲታወቅልኝ እፈልጋለሁ:: ኤርትራውያን ወንድሞቻችንና ወገኖቻችን ናቸው:: ኤርትራ የኢትዮጵያ አካል ናት ብዬ ነው የማምነው:: በሰላምና በፍቅር እንደገና አንድ እንሆናለን የሚል ትልቅ እምነት አለኝ:: ከኤርትራ ጋር የሚደረግ ጦርነት የወንድማማቾች የርስ በርስ ጦርነት እንጂ ከውጭ ኃይሎች ጋር የሚደረግ ጦርነት አይደለም::)

ወደ ፖሊስና የደህንነት አባላት ስንመጣ ግን የተለየ ሀሳብ ነው ያለኝ:: ለነርሱ በስፋት የሚጨመር ባጀት በምን መልኩ ከውጭ አገር ከሚመጣ ጥቃት ጋር ጠ/ሚሩ እንዳገናኙት አልገባኝም:: አቶ ገብሩ እንዳሉት፣ ፖሊስና የደህንነት ኃይሎች ከማብዛት ብሔራዊ መግባባት ላይ ማተኮር  የበለጠ ይበጃል እላለሁ:

በፓርላማው በነበረው ክርክር ወቅት ጠ/ሚር መለስ ድርጅታቸው ብሔራዊ መግባባት ሊኖር እንደሚገባ ሲናገሩ፣ «ብሔራዊ መግባት መፈጠር አለበት የሚባለው በራሱ ምክንያት የምንደግፈው አጀንዳ ነው» ነበር ያሉት::

እንግዲህ ከላይ ለማሳየት የሞከርኩት የኢሳቅ ራቢን ምሳሌነት እዚህ ላይ ነው የሚመጣው:: እንደ ኢሳቅ ራቢን አሁን በሥልጣን ላይ ያሉት የኢሕአዴግ ባለሥልጣናት፣ ከወጣትነታቸው ጀምሮ ጦርነትን ያዩና በጦርነት የኖሩ ናቸው:: በታሪክ ስለሚኖራቸው ቦታ፣ ስለልጆቻቸውና የልጅ ልጆቻቸው ማሰብ አለባቸው እላለሁኝ::

የጸረ-ሽብርተኝነትን አዋጅ፣ የኢትዮጵን ባንዲራ የሚመለከተው ሕግ፣ በወይዘሪት ብርቱካን ሚደቅሳ ላይ የተወሰደው እርምጃ፣ ከጊዜ ወደጊዜ በተቃዋሚዎች ላይ የሚደርሰው ወከባ . . . ኢሕአዴግን ከሕዝብ ጋር የሚያጣሉ፣ ጥላቻ እንዲስፋፋ የሚያደርጉ፣ ዜጎች የበለጠ ወደ ከረረ አቋም እንዲሄዱ የሚገፋፉ እንጂ ጠ/ሚር መለስ እንደአጀንዳ እንደግፈዋለን ያሉትን የመግባባትና የእርቅ መንፈስ የሚያመጡ አይደሉም:: ስለሆነም፣ ጠ/ሚር መለስን የምለው ነገር ቢኖር፣ «ድርጅትዎት በብሔራዊ መግባባት የሚያምን ከሆነ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተናገሩትን በሥራ ይተርጉሙት» ነው::

ጦርነት ያላወጁትን፣ በሰላምና በሕጋዊ መልክ የሚታገሉትን፣ ከኢሕአዴግ ጋር አብረው ለመሥራት የተዘጋጁትን፣ አገዛዙን እንደ «ጠላት» የሚቆጥሩ ሰዎች ፊት «ወያኔ ጠላት አይደለም» ብለው የተሟገቱትን በማጥቃት፣በማሰር፣በማፈን . . . እንዴት እርቅና ብሔራዊ መግባባት ማምጣት ይቻላል? ተናዶ የኃይል እርምጃ መውሰድ፣ በበቀል መነሳሳት፣ ሰውን ማዋረድ፣ ሰውን መስደብ፣ ሰውን መክሰስ በጣም ቀላል ነው:: በአይናችን ላይ ትልቅ ምሰሶ እያለ የሌላውን ጉድፍ ማየት፣ የተገነባውን ማፍረስ፣ አገርን ከድህነት ወደ ድህነት ማውረድ፣ጠላቶችን ማፍራት፣ሕዝብን ከሕዝብ መከፋፈል፣ ወንድምን ከወንድም ማጣላት አስቸጋሪ አይደለም::

ኢሳቅ ራቢን እንዳደረጉት ጠላት የነበሩትን ወዳጅ ማድረግ፣ የፈረሰውን መገንባት፣ አገርን ከድህነት ማውጣት፣ ችግሮችን በውይይት መፍታት፣ የተጣሉትን ማስታረቅ፣ የተበተኑትን መሰብሰብ፣ ትችትና ወቀሳን በትህትና ተቀብሎ ስድብና አሉባልታን ደግሞ ንቆ ነገሮችን በትእግስት ማሳለፍ ግን እጅግ በጣም ከባድ ነገር ነው:: ስለሆነም፣ አቶ መለስ ዜናዊና ሌሎች ባለሥልጣናት፣ ቀናውን መንገድ እንዲይዙና በፓርላማ እንደሰማነው በተግባር ለእርቅና ለብሔራዊ መግባባት መዘጋጀታቸውን ለማሳየት ተጨባጭ ሥራዎችን ለመስራት ይነሱ ብዬ ጥሪ አቀርባለሁ::

ከነዚህ ከተጨባጭ ስራዎች መካከል  በቀዳሚነት፣ በዋናነትና በአስቸኳይ ትልቅ ሥራ ሊሰራበትና እልባት ማግኘት ያለበት ጉዳይ ቢኖር የወ/ት ብርቱካን እሥር ጉዳይ ነው:: ወ/ት ብርቱካን ቃሌ በሚለው ጽሁፋቸው ይቅርታ መጠየቃቸውን በግልጽ አስቀምጠዋል፤ «በሽማግሌዎች የእርቅ ማግባቢያ መንፈስ መሰረት በፖለቲካ የተቀሰቀሰውን ክስ ፖለቲካዊ እልባት ለመስጠት በማሰብ ለእርቅ ስል ከሌሎች የፓርቲው (ቅንጅት) መሪዎች ጋር ተስማምቼ ሰኔ 11 ቀን 1999 ዓ.ም በተጻፈው ሰነድ በሽማግሌዎች አማካኝነት ይቅርታ ጠይቄአለሁ:: ይህ ብፈልግም ልለውጠው የማልችለው ሀቅ ነው» ነበር ያሉት::

ስለሆነም፣ አቶ መለስ ዜናዊ ለቢ.ቢ.ሲ. «ሀርድ ቶክ» አዘጋጅ ጋዜጠኛ ለመግለጽ እንደሞከሩት ወ/ት ብርቱካን ሚዴቅሳ ያጭበረበሩት ወይም ያታለሉት አንድም ነገር የለም:: «የይቅርታ ውሳኔ ለይቅር ተባዩ ከደረሰና ተቀባይነት ካገኘ በኋላ የይቅርታ ውሳኔ በማጭበርበር ወይም በማታለል የተገኘ መሆኑ ከተረጋገጠ የይቅርታ ውሳኔው ዋጋ አይኖረውም::» የሚለውና በጠ/ሚር መለስ የሚጠቀሰው የይቅርታ ሥነ-ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 395፣ አንቀጽ 16 (2)፣ ወ/ት ብርቱካንን በጭራሽ አይመለከትም:: «ይቅርታ አልጠየኩም» ሳይሉ፣ የማይገናኝ ይህንን የሕግ አንቀጽ እንደ ሌጦ በመተርጎም፣ በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ደጋፊዎች ያሏቸውን እኝህን የሰላም ሴት ማሰር በምንም አይነት መልኩ አገራዊ መግባባትን የሚፈጥር አይደለም::

ኢሕአዴጎች፣ተቃዋሚዎችና ሁላችንም ብሔራዊ መግባባትን በእውነት ከፈለግን፣ በሁላችንም ዘንድ የልብ መሻት ካለ፣ እንቆቅልሾቻችንን መፍታት እንችላለን:: ስለዚህ በትጋትና በቅንነት ወደ አንድነትና ወደ እርቅ ሁላችንም ልባችንን እናነሳሳ:: ኢሕአዴግ

ወ/ት ብርቱካንን በመፍታትና የፖለቲካ ምህዳሩን በማስፋት ለብሔራዊ መግባባት ያለውን ቁርጠኝነት በግልጽ ያሳይ:: እንደ ይሳቅ ራቢን ደፋርና ሰላምን የሚያበራክቱ እርምዎችን ይውሰድ::

# በታዳጊ ሀገራት የሕግ የበላይነት እንቅፋት

## - ዘላለማዊነት (Perpetuity) ማጣት -

**በግዛው ለገሰ**

ባለፈው ሳምንት በስታንፎርድ ዩንቨርሲቲ በፖለቲካ ሳይንስ ፕሮፌሰር የሆኑት የባሪ አር. ዌይንጋስት «Why Developing Countries Prove So Resistance to the Rule of Law» በ2008 ጽሁፋቸው ሁለት ማህበራዊ መስተጋብሮችን (Social Orders) ማነፃፀራቸውን አስነብበናል:: ውስን እድል ከፋች (Limited Access Orders) እና ሰፊ እድል ከፋች (Open Access Orders) የተሰኙ በመንግስት እና በሚያስተዳድረው ህዝብ መካከል ያሉ ማህበራዊ መስተጋብሮችን፣ በተለይም አንድ ህብረተሰብ ግጭት እንዳይከሰት የሚያበጀውን መላ በመመርኮዝ ልዩነቶችን ማስቀመጣቸው የሚታወስ ነው::

ውስን እድል ከፋች በሆኑ መስተጋብሮች መንግስት (የኃይለኞች ጥምረት) ግጭትን (Violence) የሚያስወግደው ተፅዕኖ ላላቸው እና ግጭት ሊፈጥሩ ለሚችሉት የህብረተሰብ ክፍሎች ልዩ መብቶችን በመስጠት ሲሆን ኪራዮችንም በመሰብሰብ ያከፋፍላቸዋል:: ከዚህም በላይ መንግስት ከህብረተሰቡ ጋር ያለው ግንኙነት በግለሰባዊ ማንነት ላይ የተመረኮዘ ነው:: በሌላ በኩል ሰፊ እድል ከፋች በሆኑ መንግስታት በፖለቲካ እና በኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ማንኛውም የህብረተሰብ ክፍል በእኩልነት የመሳተፍ እድል ሲኖረው መንግስት እና ህብረተሰቡ የሚኖረው ግንኙነት በግለሰባዊ ማንነት ላይ አይመረኮዝም::

ፕሮፌሰር ዌይንጋስት የኢኮኖሚ እና የፖለቲካዊ ልማት ሂደት ማለት ከውስን እድል ከፋች ወደ ሰፊ እድል ከፋች መስተጋብር የሚደረግ ሽግግር ነው ማለታቸውን አስነብበናል:: ለዚህ የመስተጋብር ሽግግርም በቅድሚያ ሊሰራባቸው የሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎችን ሲያስቀምጡ ዘላለማዊነት ወይም "Perptuity" አንዱ ነበር:: የዘላለማዊነት እሳቤ የመንግስት ተቋማት ይመሯቸው በነበሩ ባለስልጣናት ላይ ጥገኛ ሳይሆኑ በወቅቱ ሥልጣን ከጨበጠው ግለሰብ ህይወት ባሻገር የሚኖሩ የመንግስት መዋቅሮችን መፍጠር ነው::

ዛሬ የምናስነብባችሁ ጽሁፍም ፕሮፌሰር ዌይንጋስት የሕግ የበላይነት በታዳጊ ሀገራት ተግባራዊ ሊሆን ያልቻለበት ምክንያት ከማህበራዊ መስተጋብር ጋር የተያያዘ መሆኑን ከሚያስረዱበት ጽሁፋቸው የተወሰደ ነው።

«የሕግ የበላይነት አመጣጥ ከውስን እድል ከፋች ወደ ሰፊ እድል ከፋች ከሚደረግ የማህበራዊ መስተጋብር ሽግግር ጋር ግንኙነት አለው። ለዚህ የማህበራዊ መስተጋብር ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው ያልናቸው ቁምነገሮች የሕግ የበላይነትን ያካተቱ ናቸው። ውስን እድል ከፋች መንግስታት የሕግ የበላይነትን ዘላቂ የማድረግ ብቃት ያላቸው ተቋማትን ማቋቋም እና ተቋቁመውም ጠንክረው እንዲቀጥሉ የማድረግ ከፍተኛ እንቅፋቶች አሉባቸው። እነዚህ መንግስታት ግለሰባዊ ማንነትን መሰረት ሳያደርጉ ለህዝቡ የሚገባውን ጥቅም ማድረስ ይሳናቸዋል። በመንግስታቱ ላይም ዘላለማዊነት የለም ማለት ለረጅም ጊዜ ፖሊሲዎች ቁረጠኛ መሆን አይችሉም፤ ስለዚህም በተቋማቱ እና በፖሊሲዎች ላይ ከፍተኛ ለውጦች ሲደረግባቸው ይታያል። እነዚህ መንግስታት የሚታዘቧቸው ለውጦች የተለያየ መልክ ሲኖራቸው ለምሳሌ በቺሊ (1973) አስገራሚ መፈንቅለ መንግስትን ተከትለም ሆነ በአርጀንቲና (2001) እና በታይላንድ (1997) ከፍተኛ የገንዘብ ቀውስን ተያይዞ፣ አልያም ደግሞ ለምሳሌ በአሁኗ ሩሲያ፣ ዚምባብዌ፣ ኬንያ እና ደ. አፍሪካ ይበልጥ በተደራጀ እና ጊዜ በፈጀ መልኩ የሥርዓት ለውጥን ይታዘባሉ።

«በውስን እድል ከፋች መስተጋብሮች ውስጥ የሚከሰቱት እያንዳንዳቸው የሥርዓት ለውጦች የበላይ የሆነው ጥምረት (መንግስት) ፍላጐቶቹ በተቀየሩ ቁጥር መሪዎች የፖለቲካ መረጋጋትን ለማምጣት ተቋማትን፣ ፖሊሲዎችን ኪራዮችን፣ እና ልዩ መብቶችን እንዳስፈላጊነቱ እንዲለዋውጡ በመፍቀዳቸው የዘላለማዊነት ባህሪ አለመኖሩን ያንፀባርቃሉ። ብዙውን ጊዜ ከፖሊስ መገለባበጥ ጋር ተያይዞ እነዚህ ለውጦች ኢንቨስትመንት እና ኢኮኖሚ ላይ ከባድ ጉዳት ያስከትላሉ፤ በአንድ ሌሊት ነፃነቶችንም ሊገድቡም ይችላሉ። ከሁሉም በተደጋጋሚ የሚታየው የሕግ የበላይነትን ተግባር ላይ ለማዋል የተነደፉ ተቋማት ተጠቂ መሆናቸው ነው።»

## በምዕራቡ የሕግ የበላይነትን የሚደግፉ ሕግጋቶች፣ መብቶች እና ተቋማት ወደ ታዳጊ ሀገራት ለመምጣት ስለምን ተሳናቸው?

«ውስን እድል ከፋች የሆነ ማህበራዊ መስተጋብር ባላቸው መንግስታት ውስጥ የልዩ መብት እና ኪራይ የመፍጠር ሥርዓቶች በሰዎች ስግብግብነት ምክንያት ብቻ የተዘረጉ አይደሉም። ይልቁንም ልዩ መብት እና ኪራይ-ፈጠራ የመጡት ከግጭት ጋር ለተያያዘ ችግር መፍትሔ በመሆናቸው ምክንያት ነው። ኪራይ መሰብሰብ ኃይለኛ ግለሰቦች እና ቡድኖች ከበላዩ ጥምረት ሌሎች አባላት ጋር ተባብሮ ለመስራት ግጭት ባለመፍጠር የሚገኘውን ማበረታቻ (ሽልማት) ይሰጣቸዋል። የኪራይ ድርሻቸውን ሲወስዱም ግጭትን አይፈጥሩም። ይህ ሁኔታ ከሥርዓት አልበኝነት ጋር ሲነፃፀርም ሁሉም የህብረተሰቡ አባላት በሰበቡ ከሚመጣው ሰላም ተጠቃሚ ይሆናሉ።

«ወደዚኛው ዓለም ማሻሻያዎችን ለማራመድ የሚመጡ ሰዎች እጅግ መልካም ዓላማዎችን በመሰነቅ ነው - ኢኮኖሚስቶች የኢኮኖሚ ማሻሻያን በማስተዋወቅ፣ ዲሞክራቶች ምርጫዎች እና ዲሞክራሲን በማስተዋወቅ፣ እንዲሁም የሕግ ባለሙያዎች የሕግ ማሻሻያን እና የዜጐች መብቶች ተዘርዝረው መቀመጥን በማስተማር:: እነኚህ አራማጆች ይዘው ያመጧቸው የማሻሻያ ሀሳቦች ለዜጐች እፎይታን እንደሚሰጡ ይናገራሉ:: ነገር ግን ተሳስተዋል:: ለዚህም ምክንያቱ የማሻሻያዎቻቸው መነሻ ሰፊ እድል ከፋች ከሆነው ዓለም ነው፤ ውስን እድል ከፋች መንግስታት ከሥርዓት አኳያ ሰፊ እድል ከሚሰጡት የተለዩበትን ምክንያት ሳያገናዝቡ የሰፊ እድል ከፋች ተቋማት ስብስብን በውስን መንግስታት ውስጥ እንዳመጣጣቸው ለመዝራት ይፈልጋሉ:: በዚህ መልኩ የሚሞከሩ ማሻሻያዎች በሁለት ምክንያቶች ይከሽፋሉ - በግጭት እና ዘላለማዊ ባለመሆን::»

# የግጭትን ሚና አለመገንዘብ

«የማሻሻያ ጥረቶች ሁልጊዜ ማለት ይቻላል የውስን እድል ከፋች የፖለቲካ ሥርዓት የሚፈታውን የግጭት ችግር ይዘነጋሉ:: የልዩ መብቶች እና የኪራዮች ሥርዓት አላግባብ የሚተገበር አይደለም፤ የሚከፈልባቸው ዋጋ ከፍተኛ ቢሆንም ጠቃሚ ዓላማን ያስፈጽማሉ:: ይህንን ሥርዓት የሚያስፈጽሙ ተቋማት በግጭት አማካኝነት ለሚመጣ ችግር ተመጣጣኝ ምላሾች ናቸው:: እነዚህን ሥርዓቶች ማፈራረስ እንደ ገበያዎች፣ ምርጫዎች እና የሕግ ሥርዓት የመሳሰሉ ሰፊ እድል ከፋች ተቅማትን ለመትከል በሚደረገው ጥረት ውስጥ እንደ አንድ ተግባር አድርጐ በማካተት ሰፊ እድል ከፋች ማህበራዊ መስተጋብርን መፍጠር አይቻልም:: ይህ ለብዙ ጊዜያት ሲሞከር የቆየና ስኬታማነቱ ከስንት አንድ የሆነ ነው::

«ለኃይለኛ ግለሰቦች እና ቡድኖች ልዩ መብት መስጠት፣ ኪራይ ሰብሳቢነት እና የተሰበሰበውንም ኪራይ ግጭት እንዳይፈጥሩ ለኃይለኞቹ ማከፋፈል ግጭትን ሊያስቀር እንደመቻሉ እነዚህን አሰራሮች በማሻሻያዎች ማስቆም አንድን ህብረተሰብ የግጭቶች ስጋት እንዲገባው እና ማሻሻያዎቹን እንዲቃወም ሊያደርገው ይችላል:: ተቃርኖ የሚመጣው ከእንዲህ ያለ አሰራር ቀጥተኛ ተጠቃሚ ለሆኑ ብቻ ሳይሆን ሲበዘበዝ ለኖረው ብዙሃንም ተጽዕኖ ማሳደሩ ላይ ነው:: ለዚህም ምክንያቱ ግጭት በሰፈነበት ከመኖር ይልቅ ሰላማዊ ህብረተሰብ ውስጥ እየተበዘበዙ መኖር የተሻለ መሆን መቻሉ ነው:: ከዚህም የተነሳ የትኞቹም ሰፊ እድል ከፋች ተቋማት - ገበያዎች፣ ዲሞክራሲ አልያም የሕግ ሥርዓት - ወደ ታዳጊ ሀገራት/ውስን እደል ከፋች መንግስታት በቀጥታ እንደመጡ ሊተከሉ አይችሉም:: በመቶ ቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ዶላሮችን ቢያፈሱም፣ መልካም ዓላማ እና ምርጥ የልማት ምክር ቢያዘጋጁም የዓለም ባንክ፣ አይ.ኤም.ኤፍ. እና ሌሎቹም ስኬት ሊያሳዩ ያልቻሉበት ምክንያትም ይሄው ነው::

«ዲሞክራሲ እና ምርጫዎች ሰፊ እድል ከፋች በሆኑ ማህበራዊ መስተጋብሮች ውስጥ እንደ ዋናዎቹ የመንግስት ተቆጣጣሪዎች ሆነው ያገለግላሉ:: ምንም እንኳን ብዙ ውስን እድል ሰጪ መንግስታት ምርጫዎችን ያካሄዱ ቢሆንም - አርጀንቲና፣ ብራዚል፣ ቺሊ፣ ሕንድ እና ቬንዙዌላን ጨምሮ - በነዚህ መንግስታት የነበሩት ምርጫዎች ሙስናን የሚያስቀሩ፣ የመንግስት ሥልጣንን አላግባብ መጠቀምን የሚቆጣጠሩ፣ የዜጐችን መብቶች የሚጠብቁ፣ አልያም በጥቅሉ የሕግ የበላይነትን የሚያለመልሙ አይመስልም:: እነዚህ መንግስታት በተደጋጋሚ ለተቃዋሚዎች የመፎካከር ብቃት እንቅፋት መሆናቸውም እረግጥ ነው፤ ለምሳሌም የፕሬስ ነፃነትን በመገደብ፣ ህዝቡ ተቃዋሚ ፓርቲዎችን ወይም የሚፈልገውን እጩ ለመደገፍ በቡድን እንዳይደርጅ የመደራጀት እደልን በመንፈግ፣ አልያም ተፎካካሪ እጩዎችን ለእስር በመዳረግ::»

## ዘላለማዊ አለመሆን

«ተቋማቱ፣ ሕግጋቱ እና ፖሊሲዎቹ በወቅቱ ባሉት ባለስልጣናት ወይም የበላይ ጥምረት ማንነት ላይ የማይመረኮዙ ዘላለማዊ የሆነ መንግስት መፍጠር የሕግ የበላይነትን ለመፍጠር ማዕከላዊ ተግባር ነው:: እንደ ውስን እድል ከፋች መንግስታት በታዳጊው ዓለም ያለውም ችግር ሁሉም ማለት ይቻላል ዘላለማዊ መንግስት የላቸውም:: እጅግ ብዙ የሆኑ በሳል ውስን እድል ከፋች መንግስታት ምርጫዎችን ጨምሮ የሕግ አውጪውን፣ የአስፈፃሚውን እና የገለልተኛ ፍትህ አካሉን የሥልጣን መነጣጠል ሥርዓቶች የሚደነግጉ ሕገ መንግስቶች አሏቸው:: ችግሩ እነዚህ ተቋማት በሕገ መንግስቱ እንደተቀመጠው መስራት አለመቻላቸው ነው:: ሕግ አውጪዎች በአግባቡ የሚሰራ የፍትህ አካል በሌለበት አስፈፃሚውን መቆጣጠር አይችሉም - የሕግ አውጪውን ገደቦች በአስፈፃሚው ላይ ተግባራዊ የሚያደርግ የለም - እናም የውስን እድል ከፋች መንግስታት ሙሰኛ ዳኞች የሥልጣኖች መነጣጠል ሥርዓትን ያደናቅፋሉ::

«የዘላለማዊነት አለመኖር የፖለቲካ ባለስልጣናት የፖለቲካ ተቋማትን እና የሚያስጠብቁትን መብቶች እንዲያከብሩ የሚያስገድዳቸው ተዓማኝነት ያለው ቁርጠኝነት አለመኖር ማለት ነው:: እነኚህ ተቋማት ወይም መብቶች አልመች ሲሏቸው የፖለቲካ ባለስልጣናት እነዚህን መብቶች ችላ ይሏቸዋል፣ አላግባብ ይጠቀሟቸዋል፣ ብሎም ይሽሯቸዋል::

«በአብዛኛዎቹ ውስን መንግስታት የተቀሩት ቅድመ-ሁኔታዎችን ጨምሮ የዘላለማዊነት አለመኖር በውስን እድል ከፋች መንግስታት ውስጥ ገበያዎችን፣ ምርጫዎችን እና የፍትህ ተቋማትን እንዳመጣጣቸው የመትከል የአራት አስርት ዓመታት የማሻሻያ ሙከራ በአጠቃላዩ ታዳጊ ዓለም የተንሰራፉ ገበያዎችን፣ ንቁ ዲሞክራሲዎችን እና ገለልተኛ የፍትህ አካላትን ሊፈጥር ያልቻለበትን ምክንያት ለማስረዳት ያግዛል:: እነዚህ ማሻሻያዎች የጥቂት ዓመታት እድሜ ሊኖራቸው ቢችልም

ሊዘልቁ አይቻላቸውም፡፡ ውስን እድል የሚሰጠው መንግስት ቀውስ ሲያጋጥመው በትክክልም ወደ ጐን ይተዋሉ፡፡»

## መደምደሚያ

አግባብ ያልሆኑ አስተዳደራዊ እርምጃዎችን በማስወገድ የሕጐችን የተረጋገጡ መሆን እና በእኩል መልኩ ተፈፃሚነታቸውን የመፍጠር የሕግ የበላይነት አሰራር በተለምዶ እንደሚባለው የሕጉን ከሁሉም የበላይ መሆን ብቻ ሳይሆን ሕጉ ከዛሬ ባሻገር ለወደፊትም እየሰራ የሚቀጥልበት ጠንካራ ንጥረ ነገርንም ይጠይቃል፡፡ ይህ የዘላለማዊነት ግንዛቤን ይጠይቃል፡፡ የሕግ የበላይነትን ለረጅም ጊዜ የሚዘልቅ ለማድረግ መንግስት ዘላለም መኖር የሚችል ሊሆን ይገባል፤ ይህም ማለት የፓለቲካ ባለስልጣናት ማንነት ቦታ ሳይሰጣቸው የመንግስት ተቋማት ከፈጠሯቸው (ካቋቋማቸው) ሰዎች ህይወት በኋላም መኖራቸውን ሊቀጥሉ ይገባል፡፡ ይህንንም ብቃት በማግኘት የባለስልጣናት መለዋወጥ በተቋማት እና በመብቶች ላይ ተጽዕኖ እንዳያሳድር የፖለቲካ ባለስልጣናት እነዚህን ተቋማት እና የሚያስጠብቋቸውን መብቶች እንዲያከብሩ የሚያደርግ ተገቢ የሆነ ተዓማኝነት ያለው ቁርጠኝነት ያስፈልጋል፡፡

የፕሮፌሰር ባሪ አር. ዌይንጋስት ምልከታ የሕግ የበላይነትን በታዳጊ ሀገራት ተግባራዊ ለማድረግ ከባድ የሆነበትን፣ ብሎም ታዳጊ ሀገራት ብዙውን ጊዜ የሕግ የበላይነትን ለማስፈን የሚያንገራግሩበትን ምክንያት ይጠቁማል፡፡ በአብዛኛዎቹ ውስን እድልከፋች መንግስታት ላይ የተደቀነው ዋናው ችግር ዘላለማዊነት ማጣት መሆኑንም ያስረዳል፡፡

## ሞቲቬሽን

# የማናውቃቸው እንግዶች

# *{The Strangers}*

**በባንቺወሰን ወልደየሱስ**

ታክሲ እየጠበቀች ያለችው እጅግ በጣም ብስጭት ባለ ስሜት ነው፡፡ ከቤቷ አምራና ተውባ እንዳልወጣች ሁሉ አሁን ልብሷን ላየ «ምን ሆና ነው?!» ያሰኛል፡፡ ላለባት ሰርግ በሰዓቱ ለመድረስ እየተቻኮለች ስትሄድ ሳታስበው ውሃ የረጫትን መኪና ስታስብ ንድድ ይላታል፡፡ ወደ ቤቷ ተመልሳ ልብሷን እንዳትቀይር ጊዜ የላትም፡፡ ስለዚህ ያላት አማራጭ ወደ ፊት መቀጠል ነው፡፡ አሁንም ጉንበስ ብላ ልብሷን ተመለከተች፡፡

አኳኋኗ ተአምር ተፈጥሮ ልብሷ ወደ ነበረበት እንዲመለስላት የምትመኝ ይመስላል:: አሁንም አሁንም ጭንቅላቷን እየነቀነቀች በማዘን ላይ ሳለች የምትፈልገው ታክሲ መጣ:: የነበረውም ክፍት ቦታ ከኋላ ስለነበር ፈጠን ብላ በመግባት ላይ ሳለች ሶስተኛው ረድፍ ላይ ተቀምጦ ከነበረው አንደኛው ቦታውን ለቆላት የኋላውን ወንበር ያዘ:: እሷም በተለቀቀላት ቦታ ላይ እየተቀመጠች፣ «አስፈላጊ አልነበረም፤ አመሰግናለሁ::» አለችው ወደ ኋላ ዞር ብላ:: ያም ሰው አንገቱን በመነቅነቅ ችግር እንደሌለው ገለፀላት:: ተገረመች:: ይኽን ሰው አታውቀውም፤ ግን ይህ የማታውቀው ሰው ነው ወንበር የለቀቀላት:: ይህን ስታስብ በልብሷ መበላሸት ምክንያት የተፈጠረው ንዴቷ ረገብ አለ:: ፊቷ ላይ ጠፍቶ የነበረው ፈገግታዋ ቀስ ብሎ ታየ:: በዚህ በማታውቀው ሰው ምክንያት ጠፍቶ የነበረው ጥሩ ስሜቷ አንሰራራ፡ የእሷ መድረሻም ሳይደርስ እሱ አስቁሞ ወረደ:: በድጋሚም አመሰገነችው:: ይህቺ ሴት ከውስጧ ጋር መነጋገር ጀመረች::

«ዛሬ ያጋጠመኝ ደስታ ምንጩ የማይታወቅ ነው:: ይህን ሰው አላውቀውምና ለእኔ ምንም ነገርስ ቢሆን ለምን ያደርጋል? ግን እውነታው ይህ ለእኔ እንግዳ የሆነ ሰው አንድ ነገር አደረገልኝ። እኔም በምላሽ ከማመስገን ውጪ ምንም ልሰጠው አልችልም:: እሱ ከሰጠኝ አንፃር ሲታይ ግን የእኔ ምስጋና ቦታም ያለው አይመስለኝም:: ባልጠበኩት ድርጊቱ ተገርሜ ንዴቴን ረስቼዋለሁ:: በዚህ ሰው ተግባር ምክንያት ከቤቴ ስወጣ እንኳን ያልነበረኝ ፈገግታ አሁን ልቤም ውስጥ፣ ፊቴም ላይ እንዳለ ይታወቀኛል:: ከውስጤም ጋር ቅድም አደርግ እንደነበረው እየተነጋገርኩ ነው:: ግን ንግግሬ ከቅድሙ በጣም የተለየ ነው:: ለምንድነው ያ ሹፌር ልብሴን ያበላሸብኝ? እያልኩ ሳይሆን ያለሁት፣ ይሄ የማላውቀው ሰው ስላደረገው ድርጊት ነው እያሰብኩ ያለሁት:: ተግባሩ ትንሽም ትሁን ትልቅ በደንብ ልብ አላልኩትም:: ከልቤ ሊወጣ ያልቻለው ነገር ግን እሱ እኔን አያውቀኝም፣ እኔም አላውቀውም:: እንደዛም ሆኖ ግን ከወንበሩ ተነስቶልኛል:: እኔ ስለዚህ ተግባሩ ሳስብ ምናልባትም እሱ ትዝም አይለው ይሆናል:: ጥሩ ነገር የተደረገልኝ እኔ ነኝና አስታውሰዋለሁ::»

አናይም እንጂ አትኩረን ብናይ ኖሮ፣ ዓለም መልካም ነገር በሚያደርጉ እንግዶች የተሞላች ነች:: እስኪ እነዚህን ሰዎች እኛ የት እናውቃቸዋለን? ስማቸው ማን ነው? ምንድን ነው የሚሰሩት? የት ነው የሚኖሩት? ቤተሰባቸው ምን ዓይነት ነው? እነሱስ ምን ዓይነት ሰው ናቸው?

- እኛ አስቀድመን እንድናልፍ የሚያደርጉን የመኪና አስሽከርካሪዎች፤
- ዕቃ ይዘን ሳለ ሽክሙን ለመጋራት የሚጠይቀን ሰው፤
- እኛ ሳንጠይቅ ከወንበሩ በመነሳት ቦታ የሚለቅልንን፤
- በእጃችን የያዝናቸው መጽሐፍቶች ወይም ወረቀቶች መሬት ላይ ወድቀውብን ለማንሳት ስናጐነብስ የወደቁትን ለማሰባሰብ ጐንበስ የሚሉ፤

- በጭራሽ ከዛ ቀን በፊት አይተነው የማናውቅ ሰው ልብን በሚነካ ፈገግታ ሰላም ሲለን ወይ ቻው ሲለን፤
- ልጃችንን ከት/ቤት የምናመጣበት ሰዓት በስራ ምክንያት አልፎ ት/ቤት ስንደርስ አንዲት እናት ከራሷ ልጅ ጋር ልጃችንን የምታጫውተውን፤
- የምንወደውን ኬክ ለማዘዝ ኬኮቹ ወደተደረደሩበት ተጠግተን እኛ ከምንወደው የቀረ አንድ ኬክ ስናሳይና ልክ በዛ ደቂቃ ያንኑ ኬክ የመረጠ ሌላ ሰው አጠገባችን ቆሞ ስናይና ምርጫውን ትተን ልንሄድ ስንል ያ የማናወቀው ሰው የቀረውን ሁለታችንም የምንፈልገውን አንድ ኬክ ለእኛ የሚተውልን፤
- በጣም እንደቸኮልን አኳኋናችን በጣም ከማስታወቁ የተነሳ ወይ ሊፍት ላይ ሊሆን ይችላል ወይም ትራንስፖርት ላይ ቅድሚያውን ለእኛ የሚሰጠንን፤
- ሆስፒታል ውስጥ ሆነን ህክምና እየተደረገለት ያለውን ጓደኛችንን ወይም ዘመዳችንን እያሰብን ኩርምት ባልንበት ሁኔታ መጥቶ የራሱን እዛ መገኘት ምክንያት ችላ ብሎ እኛን የሚያጽናናንን፤
- በስህተት ስልክ ሌላ ቦታ ደውለን በሌላኛው መስመር ላይ የሚገኘው ሰው በትህትና እንደተሳሳትን የሚነግረን ሰው፤

ከነዚህ ሰዎች ጋር ባንተዋወቅም እንኳን ድርጊታቸው ትንሽም ይሁን ትልቅ እኛን ባለንበት ቆም እንድንል ያደርጋል፡፡ ልክ ለማያውቁት ሰው ያደረጉትን ተግባር ስናይ አግራሞትና መደነቅ ልባችንን ይነካዋል፡፡ ከእነዚህ ሰዎች ጋር ከተለያየንም በኋላ ቢሆን እነሱ ቢረሱትም እኛ ግን ድርጊታቸውን እናስታውሰዋለን፡፡ አዝነን፣ ተረብሸን፣ ችግር አጋጥሞን ወይም አንድ ነገር ሆነን ከነበር የነዚህ የማናውቃቸው ሰዎች ተግባር ሕይወትን በአዲስ አቅጣጫ እንድናይና ከልብ የመነጨ ፈገግታ ፈገግ እንድንል ያደርገናል፡፡